# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ደ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢ.ትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ሳቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢ.ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

# ትንሣኤ



አልቦ እምቅድሜሁ ወአልቦ እምድኅሬሁ ፤ ማኅሌታይ ሰብአ ዘከማሁ ፤ ያሬድ ካህን ይኬልህ ትንሣኤሁ ።
ከእርሱ በፊትና በኋላ እንደ ያሬድ ያለ ዜማዊ ሰው አልተነሣም ፤ ካህን ያሬድ ትንሣኤውን ይሰብካል ።

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም    ቁጥር 32    ግንቦት ፲፱፻፸፱ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረ ጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።


አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ


# ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ርእሰ አንቀጽ | ፪ |
| መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት | ፫ |
| ልደታ ለቅድስት ድንግል ማርያም | ፬ |
| ቅዱስ ያሬድና ትምህርቱ | ፭ |
| ይህን ያውቁ ኖረዋል? | ፯ |
| የጥንታዊው ደብረ ሊባኖስ ገዳም | ፰ |
| ምን እንርዳዎ | ፲ |
| የሴቶች ዓምድ | ፲፪ |
| የሃይማኖት ዓምድ | ፲፬ |
| ሊቃውንቶቻችን | ፲፯ |
| የድሆች ጠበቃ | ፲፱ |
| ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ዓርጋለሁ | ፳፪ |
| የጤና ዓምድ | ፳፫ |

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ሰይጣን ይዞአቸዋል የሚባሉ ሰዎች በሚለፈልፉበት ጊዜ የሚካኤልና የገብርኤልን ስም አይጠሩም ፤ እርግጥ ለቅቶ በሚሄድበት ጊዜ የሚካኤልንና የገቤርኤልን ስም እየጠራ ይገዘታል ። ነገር ግን በናዝሬት አካባቢ ሰዎች ተሰብስበው የሚካኤልና የገቤርኤልን ስም እየጠሩ ሲያጓሩ ሰማሁ ። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ?

አፀደ አለም፣የፖ.ሣ.ቁ.30149፣አ.አ

• ጥያቄዎ ብዙ ነበር ግን ተመሳሳይ ስለሆነ በአንድ ተጠቃልሎአል ። ሰይጣን ደፋር ስለሆነ በቅዱሳን መላእክት እየተመሰለ ሰዎችን የሚያታልል መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎአል ። "ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና" ተብሎ የተጻፈውን ቢመለከቱ በናዝሬት ያዩት ነገር ላይ ገርምዎ ይችላል 1 ቆሮ.11፥14

ooo

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

እግዚአብሔር በኢትዮጵያ የሠራቻው ብዙዎች ድንቆችና ተአምራት አሉ ለምን በመጽሔታችሁ አታወጡአቸውም ? ሁለተኛ የንስሐ አባት ስለመያዝ መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም ይህ ነገር የቤተ ክርስቲያን ትእዛዝ ነው? ወይስ ከጌታ የተሰጠ ትእዛዝ ነው?

ተሾመ ዘአማኑኤል ከዶዶላ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት ቤት ባሌ ዶዶላ

• እግዚአብሔር በኢትዮጵያ የሠራቻውን ተአምራት እርስዎም ቢጠቁሙን በመጽሔታችን እናወጣለን እስካሁን በበኩላችን ያየናቸውንና የሰማናቸውን አውጥተናል ።

የንስሐ አባት ስለመያዝ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎአልና የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመልከቱ ማቴ. 16፥19 ማቴ.18፥18 ዮሐ. 20፥21-23 ። 1ቆሮ 5.4-5 ። 2ቆሮ 4.6-7 ። የንስሐ አባት እንደሚያስፈልግና ኃጢአትንም ለእርሱ መንገር እንደሚገባ የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመልከቱ ማቴ .8.4 ሉቃ.17፥12-14 ።ይህ ከሆነ የንስሐ አባት መያዝና ኃጢአትን ለካህን መናዘዝ የጌታ ትእዛዝ ነው ።

ooo

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ በክርስቶስ የከበረ ሰላምታዬን አቀርባለሁ እኔ የምጠይቀው ጥያቄ ቢኖር የቅዱስ ጊዮርጊስ እለት ወይም የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሌሎችም ጻድቃን ምን እንደሠሩ እንድናውቅ በየወራቸው የቅዱሳን ታሪካቸው ገድላቸው እውጭ በአትሮንስ ተዘረግቶ ሲተረጐም ። ትምህርት ለሌለን ትምህርት ፡ ጽናት ለሌለን ጽናት ፡ስለ ማይሠጠን የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ቢያስቡበት መልካም ነው እላለሁ ። ትንሣኤስ ስለዚህ ነገር ምን ይላል?

ከመጽሔታችሁ ተከታታይ አንዱ ተማሪ መኰንን ጌታነህ
ኰልፌ እህል በረንዳ አ.አ

• የቅዱሳን ገድልና ተአምር በተወሰነ ጊዜ በዕለት በዓላቸው ይነበባሉ ። የቅዱሳንም ሥራ ይነገራል ። ጠያቂው እንደ ጠየቁት ስለሃይማኖት ትምህርትና ጥናት መሠረቱ የወንጌል ቃል ነው ።ስለዚህ የቅዱሳንን ምሳሌነት ለመያዝና ገድላቸውን እናነባለን እምነታችንን ለማጽናት ወንጌልን እንሰብካለን ።

ooo

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስስምሰላምለናንተይሁንእላለሁ ብመንፈስሐሳቢየመላእክትንየቅዱሳንን ምግባርና ሥራ ስሰማ በጣም እደሰታለሁ ስእላቸውንም በማየት ደስታዬ የበዛ ነው ግን ስዕል ስመለከት የመላእክቶች ክንፍ ሁለት ብቻ ሲሆን አቡነ ተክለ ሃይማኖት 6 ክንፎች አሉአቸው ።

እንዴት ከመላእክቶች የርሳቸው በለጠ? ብጠይቅ ስአሊው እርሳቸውን ከፍ ለማድረግ እንጂ ክንፋቸው ከሁለት በላይ አይመስለኝም ይሉኛል ምንጊዜም እውነቱ ከናንተው ስለሆነ መልሱን በናፍቆት እጠብቃለሁ ማወቅ እሚገኘው ከመጠየቅ ስለሆነ በምሣሣተው ይቅርታ ።

ፈቃደ ተድላ

• ፈቃደ ተድላ በመጀመሪያ ስለ ጥያቄዎ እጅግ እናመሰግናለን፡-ከመላእክትም ቢሆን ስድስት ክንፎች የአሉአቸው መላእክት አሉ ። ለምሳሌ ሱራፌልና ኪሩቤል(እለ ስድስቱ ክንፊሆሙ) ስድስት ክንፍ እንዳላቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ይገኛል ኢሳ 6፥2-8

ስለዚህ አቡነ ተክለሃይማኖት እንደ ኪሩቤል ስድስት ክንፍ ተሰጥቶአቸው ይሆናል ።

ooo

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በቅድሚያ ሁሉን በሚችልና ለዘለዓለም ህያው ሆኖ በሚኖረው በእግዚአብሔር ስም የከበረ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ።

ከሰላምታዬ ቀጥዬ ልገልፀው የፈለግሁት ከዚህ የሚከተለው ነው ።

ማርቆስ 16 ቁ16 ላይ ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል ይላል ስለዚህ አምነውም ሳያምኑም የማይጠመቁ አይድኑም ማለት ነው ? እባክዎት የዚህን መልስ አብራርተው ይመልሱልኝ ስል እጠይቅዎታለሁ ።

ወ ት አርሴማ ገብሩ
ከአዲስ አበባ

• ወ ት አርሴማ ገብሩ እንደ ክርስትና ሃይማኖት ያላመነና ያልተጠመቀ እንደማይድን ተደጋግሞ በቅዱስ ወንጌል ተገልጦአል ። ለምሳሌ አንቺ ከጠቀሽ ሌላ ጥቅስ በዮሐንስ ወንጌል 3.ቁ5"... ...ሰው ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም" ይላል ። እኛም በወንጌሉ ቃል እናምናለን ።

ooo

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

. በሐዋርያት ጊዜ እጅ እየጫኑ መንፈ

ወደ ገጽ ፲፫ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

✓

## ርእሰ አንቀጽ

# በረከተ ያሬድ

አንዱ ቄስ ሌላውን ቄስ መስቀል በሚያሳልምበት ጊዜ "ስእመተ ሚመተ እዴሁ ለአቡነ ጴጥሮስ" በማለት ያሳልመዋል ፣ "በምድር የፈታኸው በሰማይ የተፈታ ይሁን በምድር ያሰርኸው በሰማይ የታሠረ ይሁን" ተብሎ ለጴጥሮስ የተሰጠው የሥልጣነ ክህነት ባለቤት ነህ ሲለው ነው ፤ እንዲሁም ዲያቆኑን ሲባርክ "በረከተ እስጢፋኖስ ይኅደር በላዕሌከ" በማለት ይባርከዋል ፣ እስጢፋኖስ የመጀመሪያው ዲያቆን ከመሆኑም በላይ በቅንነት ፍጹም አገልግሎትን አገልግሎ ፍጹም በረከትን እንደተቀበለና ለነፅሮተ ስሉስ ቅዱስ እንደበቃ አንተም ፍጹም አገልግሎትን አበርክተህ ፍጹም በረከትን እንድትቀበል ሁን ሲለው ነው ።

በዘንግ እየዘመመ በጽናጽል እያመረገደ የሚዘምረውን ካህን ደግሞ "በረከተ ያሬድ ይኅደር በላዕሌከ" በማለት ይባርከዋል በመዝሙር ማመስገን ፣ በመዝሙር መጸለይና ማስተማር የጀመረ ያሬድ በመሆኑና በዚህም ፀጋ ፣ረድኤተ እግዚአብሔር ስላደረበት የእርሱን በረከት ያሳድርብህ ሲለው ነው "በረከተ ያሬድ" የሚለው ርእስ ከዚህ በላይ በተገለጸው ብቻ የሚወሰን አይደለም ። ቅዱስ ያሬድ ለኢትዮጵያ ያበረከተውን ትምህርት በቅደም ተከተል ለመግለጽ የሚያስችል ነው ።

ቅዱስ ያሬድ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ያበረከተው ትምህርት በታሪክና በባህል አንጻር ሲመዘን ኢትዮጵያን ከአሳወቁአት ነገሮች የመጀመሪያው ነው ፣ የያሬድ ትምህርት በቅርጹና በይዘቱ በዓለም ተወዳዳሪ የሌለው አስደናቂ ትምህርት እንደሆነ ታውቆአል ።

የያሬድ ትምህርት በቃናውና በጣዕመ ዜማው በዓለም ከሚገኙት መዝሙራት ልዩ ነው ። ልዩ ያደረገውም 1-ስልተ ዜማው ነው ይኸውም ግእዝ ዕዝልና አራራይ ይባላል ፣ እንደ መዝሙር እንደ ጊዜው ሁኔታ በሦስቱም የዜማ ስልቶች ይዘምራል ።

ሀ-ቅድመ ቁርባን የሚጸለይና የሚዘመር መዝሙር ፣ ዚቅ አንገርጋሪ ፣ እስመ ለዓለም አቡን ዕዝልና ሰላም ነው ።

ለ- ድኅረ ቁርባን የሚጸለይና የሚዘመር ዝማሬ ይባላል እርሱም ስለ ሥጋ ወደሙና ስለ ነገረ መስቀል የሚዘመር ነው ።

ሐ- ለሙታን የሚጸለየውና የሚዘመረው መዋሥዕት ይባላል

2- በየጊዜያቱ የሚጸለይና የሚዘመር ስብሐተ ማኅሌት አለ ።

ሀ- እንደ ጊዜው ሁኔታ ፣ በጾም ቀናት ፣ በዓመልት ፣ ጾም ባልሆነ ቀናት በሌሊት ይፈጸማል ይኸውም በአጠቃላይ ማኅሌት ይባላል ።

ለ- በነግህ የሚዘመርና የሚጸለይ ስብሐተ እግዚአብሔር "ስብሐተ ነግህ"

ሐ- በሠርክ የሚፈጸመው ደግሞ ዋዜማ ይባላል ።

3- በየወቅቱ የሚዘመር መዝሙርን ወቅቶችን እያስመለከተ በመዘመር ለቤተ ክርስቲያን ያበረከተው መዝሙር አገሪቱን ከሌሎች አህጉር ቤተ ክርስቲያኒቱን ም ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ለይቶ አሳውቆአታል ።

ይኸውም፡- ሀ- ክረምትን

ለ-መጸውን

ሐ- ሐጋይን

መ-ፀደይን በማስመልከት የመዝሙር ድርሰቱን አበርክቶአል ። ከዚህም ጋር ወርኀ ጽጌ ወርኀ አስተርእዮና ወርሃ ሥጋዊ ወርኀ ትንሣኤ ለመሳሰሉት ሁሉ ልዩ ልዩ መዝሙርን አበርክቶአል ።

4-በተለያዩ በዓላት ቀን የሚጸለዩና የሚዘመሩ ትምህርቶች ፡-

ሀ- በጌታ በዓላት

ለ- በእመቤታችን በዓላት

ሐ- በቅዱሳን መላእክት በዓላት

መ- በቅዱሳን ሰማዕታትና ጻድቃን በዓላት



ሠ- ስለመስቀልና ቤተ ክርስቲያን የሚጸለዩና የሚዘመሩ መዝሙሮችን አዘጋጅቶአል ፣ ቅዱስ ያሬድ ያበረከተው መዝሙር ሁለንተናው ጸሎት ቢሆንም ቅሉ በተለይ ከመዝሙረ ዳዊትና ከሌሎችም መጻሕፍት አውጣጥቶ ለጸሎት ያዘጋጃቸው አሉ ። ለምሳሌ ከሥተት ወተጋብእና መሐረነ አብ የመሳሰሉት ናቸው ።

ቅዱስ ያሬድ ድርሰቱን ያዘጋጀው ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳን አውጣጥቶ ነው ፣ ድርሰቱንም ተቀባይነት ያለውና ተወዳጅ ያደረገው ጣዕሙ ብቻ ሳይሆን ኃይለ ቃሉና ምሥጢሩም ከብሉይ ፣ ከሐዲስና ከቤተ ክርስቲያን አባቶች ትምህርት ጋር አንድ መሆኑ ነው ። ስለሆነም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ያሬድን ከታላላቁ የቤተ ክርስቲያን አባቶች እንደ አንዱ አድርጋ ትቀበለዋለች ። በስሙም ጽላት አስቀርጻ ቤተ ክርስቲያን አሳንጻ አማላጅነቱን አምና ብሔራዊ ቅዱስ እንደሆነ ትቀበለዋለች ።

ስለዚህም «ያሬድ ማኅሌታይ ለእግዚአብሔር ካህኑ ስብሐተ ትንሣኤ ዘይዜኑ አሪት ቶታኑ ወወንጌል አሣዕኑ፣ ትርድአነ ንዑ በህየ መካኑ ....» ወደ አማርኛ ሲመለስም የጫማህ ማዘቢያ ኦሪት ፣ የእግርህ መጫሚያ ወንጌል የሆነና የትንሣኤን ክብር የምታስተምር የእግዚአብሔር አገልጋይ ማኅሌታይ ያሬድ! በዚህ ቦታ ትረዳን ዘንድ ና!..." ብላ በመጸለይ ተራዳኢነቱንና አማላጅነቱን ታስተምራለች ።

ቅዱስ ያሬድ በመንፈስ እግዚአብሔር እየተቃኘ ያበረከተውን ስብሐተ ማኅሌት በተገቢው ዕለትና ቦታ የሚዘምሩ ካህናት መንፈሳዊ በረከትን ያገኛሉ የቅዱስ ያሬድ ስብሐተ ማኅሌት ያለማቋረጥ የሚደረስባት ቤተ ክርስቲያንም የመንፈሳዊ በረከት አውድማ ናት ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ያሬድ በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ በአበረከታት ስብሐተ እግዚአብሔር ስትገለገልበት ስትከበርበትና ለተከታዮችዋም(ለአገልጋዮችዋ) መንፈሳዊ በረከትን ስታደልበት ኑራለች ፣ ወደፊትም ትገለገልበታለች ። ታዲያ

1ኛ በቅርስነቱ የሚያኮራ ፣ 2ኛ በጸሎትነቱና በትምህርቱ መንፈሳዊ በረከትን የሚያስጥ ይህ ያሬዳዊ በረከት እንዳይቋረጥ ቤተ ክርስቲያን በጥብቅ ልታስብበት ይገባል ።

# መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት

እሳት በዚህ ዓለም ካሉት ነገሮች ሁሉ ለሰው ሕይወት በመጥቀም በኩል ከፍተኛ ደረጃ የያዘ መሆኑ ይታወቃል ።የእሳት ጥቅም ከመታወቁ በፊት ይኖሩ የነበሩት የጥንት ሰዎች የለቀሙትን የዱር ፍሬና የገደሉትን የአውሬ ሥጋ የሚቀቅሉበትና የሚጠብሱበት እሳት በማጣታቸው ከፍ ያለ ችግር ይደርስባቸው ነበር ። የሚሞቁትም በማጣታቸው በብርድ ከመሠቃየታቸውም በላይ የእሳትን ብርሃን ባለማግኘታቸው በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ስለሚኖሩ ኑሮአቸውም ሕይወታቸውም ጨለማ እንደነበር ይታወቃል ።

እሳትን ካገኙ ወዲህ ግን የለቀሙትን የዱር ፍሬና የገደሉትን የዱር አውሬ እያበሰሉና እየቀቀሉ መመገብ ስለጀመሩ ኑሮአቸው መሻሻል ጀመረ ።በሙቀቱም ሆነ በብርሃኑ ከብርድና ከጨለማ ለመላቀቅ ችለዋል ። በጠቅላላው የሰለጠነውም ዓለም ቢሆን ያለ እሳት ኑሮውን ሊገፋ ሕይወቱን ሊመራ ስላልቻለ ቤቱን በሙቀት መስጫ እያሞቀ በብርሃኑ እየተጠቀመ ምግቡን በማብሰል በእሳት ኃይል ይጠቀማል ።

በዚህ አኳኋን እሳት ሦስት ጠባዮች እንዳሉት ለማወቅ ይቻላል 1ኛ ብርሃን 2ኛ ሙቀት 3ኛ ዋእይ በሙቀቱ ተፈላጊውን ነገር ያሞቃል ። በብርሃኑ ጨለማን ያስወግዳል ። በዋዕዩ እርጥቡን ያደርቃል ደረቁን ይበላል የሰውን ልጅ ተቃዋሚ የሆነውን ቆሻሻ ሁሉ አቃጥሎ በማጽዳት ጤንነትን ያስገኛል ጽዳትን ይሰጣል ። ከዚህም የተነሣ ያለ እሳት የሰው ሕይወት ሊንቀሳቀስ ኑሮው ሊሟላ እንደማይችል የታወቀ ነው ።

መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት የሚለውን ደግሞ እንመልከት ያለ መንፈስ ቅዱስ ዕርዳታና ያለመንፈስ ቅዱስ አጽናኝነት የሰው ሕይወት ሊንቀሳቀስ ሊራመድ አይችልም ያለ መንፈስ ቅዱስም ኃይል የሰው ሕይወት ሠርቶ ማሠራት አውቆ ማሳወቅ ተምሮ ማስተማር አይችልም የመንፈስ ቅዱስ እሳትነት በሰው ሕይወት ውስጥ ገብቶ ከተቀጣጠለና ብርሃኑን ካበራ ግን ሌላውን እንደራሱ ይወዳል ራሱን ብቻ ከማገልገል ይልቅ ሌላውን ማገልገል ደስ ይለዋል ። ከመረዳት ይልቅ መርዳትን ይወዳል ። በጠቅላላው ለማንኛውም በጎ ሥራ ሁሉ እራሱን መሥዋዕት አድርጎ ያቀርባል ።

የመንፈስ ቅዱስ እሳትነት በውስጡ ያልተቀጣጠለና በልቡ ያልበራ እንደሆነ ግን እራሱን ይወዳል ሌላውን ይጠላል ከፍ ያለ ተአምራት ሲደረግ ቢመለከት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሕሙማን ሲፈወሱ ቢያይም ለጊዜው ከመደነቅ በቀር ወዲያው ስሜቱ ይቀዘቅዛል ።ይኸውም በደቀ መዛሙርቱ ሊታወቅ ይችላል ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን ከመቀበላቸው በፊት ጌታችን ኢየሱስ ክርስ

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ልደታ ለቅድስት ማርያም

የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሐረገ ትውልድ በቡልይ ኪዳን በትንቢትና በምሳሌ ፣ በሐዲስ ኪዳንም ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ሥጋዊ ልደት በተነገረበት ቦታ ተጽፎ ይገኛል ።

ለምሳሌ፡- "የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ ማቴ. 1.1፡

"በሥጋ ከዳዊት ዘር ተወለደ" ሮሜ 1፡1፡

"የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም" ዕብ. 2፡16 እነዚህና የመሳሰሉት ጥቅሶች ሁሉ በሥጋ ከቅድስት ድንግል ማርያም ስለተወለደው እግዚአብሔር ወልድ ቢያመለክቱም በመሠረቱ የድንግል ማርያም ልደት ከአብርሃምና ከዳዊት ወገን እንደሆነ በቂ ማስረጃ ናቸው ።

ከዚህም ሌላ ነቢያት በትንቢት ከተናገሩአቸው ምሳሌዎች መካከል አንዳንቹ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ልደት የሚያመለክቱ መሆናቸውን የዘመነ ሐዲስ ሊቃውንት ተርጉመዋል ። ለምሳሌ፡-

"በትር ከእሴይ ግንድ ይወጣል ፣ ከሥሩም ቁጥቅዋጦ ያፈራል" ኢሳ. 11፡1 በማለት ነቢዩ ኢሳይያስ የተናገረውን ምሳሌ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ (500)

"ትወጽእ በትር እምሥርወ እሴይ ወየዐርግ ጽጌ ይእቲ በትር አምሳለ ማርያም ቅድስት ይእቲ ወጽጌ ዘወጽአ እምኔሃ አምሳሉ ለወልድ… ብትር ከእሴይ ሥር ትወጣለች አበባም ከእርስዋ ይወጣል በትርዋ የቅድስት ማርያም ምሳሌ ናት ። ከእርስዋ የወጣው አበባም የወልድ (ክርስቶስ) ምሳሌ" ነው በማለት ተርጉሞታል ። (ድጓ ዘማርያም) ከያሬድም በፊት ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም (400) ከዳዊት ዘር የተገኘሽ ዘመድ አንች ነሽ" በማለት ይህን የኢሳይያስን ምሳሌ በጉልህ ትርጓሜ አስረድቶአል ። (ኤፍሬም 6፡4) እንግዲህ በሁለቱ መንፈሳውያን ሊቃውንት ትርጓዋሜ መሠረት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በአንድ በኩል ከቤተ ይሁዳ ከእሴይ ዘር ከዳዊት ወገን መወለድዋ የተረጋገጠ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ከቤተ ሌዊ ከአሮን ወገን ለመሆንዋ የቀደሙን ሊቃውንት የቤተ ክርስቲያን አባቶች የጻፉልንን ማስተዋል ይጠቅማል ። በላይ የጠቀስነው ታላቁ የኢትዮጵያ ኦ.ተ. ቤ. ክርስቲያን አባት ቅዱስ ያሬድ፡-

"…በሩካቤ ዘበሕግ እለ ወለድዋ
እምቤተ ክህነት ወመንግሥት ዘነ
ረይዋ
ይእቲኬ ማርያም ድንግል
በሕጋዊ ሩካቤ የወለዱአት
ከቤተ ክህነትና ከቤተ መንግሥት
የመረጡአት
ድንግል ማርያም ናት" (ድጓ ዘነ
ሐሴ ማርያም)

ሲል እመቤታችን ከቤተ ይሁዳ እንደ ተወለደች ከቤተ ሌዊም መወለድዋን አብራርቶ ተናግሮአል። በሌላም ቦታ "…እምዘመደሙ ለካህናት እንተ ሡረፀት ለሕይወት…" ከካህናት ወገን ለሕይወት ተወለደች የሚለው ቃል ከቤተ ክህነት ያላትን ሐረገ ትውልድ በተጨማሪ ያስረዳል ። በዚህ አንጻር ሌሎች የውስጥና የውጭ ሊቃውንት ተናግረዋል ጽፈዋልም ።

ቅድስት ድንግል ማርያም መቼ በየት ከእነማን ተወለደች ? ትውፊታዊ ትምህርት እንደሚያስረዳን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግንቦት አንድ ቀን በ15 ዓ.ዓ. ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ተወለደች ። ወላጆችዋም ኢያቄምና ሐና ይባላሉ ፣ ኢያቄም ከቤተ ይሁዳ ሲሆን ሐና ከቤተ ሌዊ ናት ። እመቤታችን የተወለደችበት ሀገር ናዝሬት ነው ። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የቅድስት ድንግል ማርያምን ልደት በመስከረም 10 ቀን ያከብራሉ ። ይህም ሀሳብ በቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ "ወቦ እለ ይቤሉ አመ ዐሡሩ ለመስከረም ልደታ ፣ መስከረም ፀሥር ቀን ልደትዋ ነው የሚሉ አሉ" በማለት ተመዝግቦ ይገኛል ። ትውፊት እንደሚያረጋግጥ ኢያቄምና ሐና እመቤታችንን ከመውለዳቸው በፊት ልጅ አልነበራቸውም ። በዚህም ምክንያት ልጆች ያሉአቸውን ሰዎች በመመለከት "የእኛ ተፈጥሮ ከምን ነው"? እያሉ እጅግ ያዝኑ ነበር ያሳዝኑአቸው ከነበሩ ነገሮችም አንዱ ልጆች ባሉአቸውና በሌሎአቸው ሰዎች መካከል የሚፈጸመው አሪታዊ ሥርዐት ነበር ። ለምሳሌ ልጆች ለአሉአቸው ከፍተኛ በረከት ሲሰጥ ልጆች ለሌሎአቸው አነስተኛ ይሰጥ ነበር ። ከዚህም ሌላ፡-

"ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው" (መዝ.126.3)

"እግዚአብሔር የሚፈልገው ምንድን ነው ? ዘር አይደለምን" (ሚል. 2፡15) የሚለውን ቃለ መጽሐፍ ሲያነቡ እግዚአብሔር ሕይወት ላላቸው ፍጥረቶች ሁሉ የሚሰጣቸው ታላቁ የዘር በረከት እንደቀረባቸው እያሰቡ እጅግ ከፍ ያለ ኀዘን ሳይሰማቸው እንዳልቀረ መገመት አያዳግትም ። ከዚህም የተነሣ ልጅ እንዲያገኙ ለእግዚአብሔር ተሳሉ ስእለታቸውም "ልጅ ስጠን" ማለት ብቻ አልነበረም የሚፈልጉትን ልጅ ለይተው ተስለዋል ። ለምሳሌ የተባረከች እግዚአብሔርንና ሰውን የማያሳዝን (የማታሳዝን) በእግዚአብሔርና በሰው ፊት በጥበብና በሞገስ የሚ(የምት) መላለስ ልጅ ለማግኘት ስእለታቸውን ለይተው ለእግዚአብሔር አቅርበዋል ስእለታቸው ይህ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር በያቅርታው ቢጎበኛቸውና ልጅ ቢወልዱ ልጁ ለእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሚሆን ወስነው ነበር ።

ወደ ገጽ ፳፫ ዞሯል



# ቅዱስ ያሬድና ትምህርቱ

አልቦ እምቅድሜሁ ወአልቦ
እምድኅሬሁ ፡-
ማኅሌታይ ሰብእ ዘከማሁ ፡-
ያሬድ ካህን ይኬልህ ትንሣኤሁ
ኢየዐዱ እንስሳ ወሰብእ እመነ ሠላስ
ዜማሁ ፡- (ድጓ ግንቦት 11 ቀን)

ከእርሱ በፊትና በኋላ በኢትዮጵያ ቤ. ክርስቲያን እንደ ያሬድ ያለ ዜማዊ ሰው አልተነሣም ። ያሬድ ካህን ትንሣኤውን ይሰብካል ።

እንስሳ ፣ ሰውም ከሦስቱ የያሬድ ዜማዎች አይወጣም ።

እንዲህ ተብሎ የተደረሰለት ቅዱስ ያሬድ ፡- አክሱም ላይ ከቤተ ነፋስ ወገን ተወለደ ።በዚያ ዘመን ስመ ጥሩ መምህር ለነበረው ለጌዴዎን የእህቱ ልጅ ነው ያሬድ የኢትዮጵያን ዜማ መሥራች እንደሆነ በብሔራውያን ሊቃውንት በተመሰከረለት መሠረት በዓለም ሁሉ ታውቆአል ።

በስንክሣርና በገድሉ ላይ ተጽፎ እንደሚገኝ ፣ በልጅነቱ ፊደል ሲማር 7 ዓመት አልጠናልህ ብሎት ሲቸገር አጎቱ ጌዴዎን የተባለ መምህር ከፋኛ ገረፈውና ማይኪራህ ወደምትባል እከተማው ዳር በስተሰሜን ወገን ወደምትገኝ ቦታ ሄዶ ሲያለቅስ ፣ አንድ ትል እንጨት ላይ እወጣለሁ እያለ ሲሞክር 6 ጊዜያት ወደቀና በ7ኛው ጊዜ ከዛፉቱ ላይ ሲወጣ አየ ።

ከዚህም በኋላ ባየው ነገር ተጽናንቶ ወደ ትምህርት ቤቱ ተመለሰና ትምህርቱን ሲጀምር በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾለት 81 መጻሕፍትን ዐወቀ ።

እንዲሁም አንድ ቀን ሦስት ወፎች አየና በእነርሱ አማካይነት በሰማይ ላይ 24ቱ ካህናተ ሰማይን አይቶ ምስጋናቸውን መዝሙራቸውንም በመስማት ስለተመሰጠ ፣ በሦስቱ ዎፎች መልክና ድምፅ ዜማውን "ግዕዝ ፣ ዕዝል ፣ዓራራይ" በሚል ስልት ባህሉን አወጣ ።

ወዲያውም "ሙራደ ቃል" በተባለው በአክሱም አደባባይ" ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ፡ ቀዳሚሃ ለጽዮን ሰማየ ሣረረ ወዳግም አርአዮ ለሙሴ ዘአመ ይገብር ግብራ ለደብተራ ።

ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ የጽዮንን መጀመሪያነት በሰማይ ላይ ሠራ ዳግመኛ ግን የድንኳኒቱን ሥራ እንዴት እንደሚሠራ ለሙሴ አሳየው ሲል በዜማ ጮኸ ።

ይህም ዜማ ሰማያዊ ድምፅ ስለተባለ' "አርያም" ተብሎ ተጠራ ። ቃሉ የወረደለት አደባባይም ሙራደ ቃል" ተሰኘ ይህም ቀን ፣ የበዐለ ስብከት እሑድ ዕለት እንደነበረ በዜማ ባህል ይተረካል ።

ከዚህም በኋላ ያሬድ ብዙ ግጥሞችንና ድርሰቶችን እያዘጋጀ የዜማን ስልቶች አበጀላቸው ። ከያሬድ በፊት በቤ. ተክርስቲያን ውስጥ መጻሕፍትን ማንበብ ፡ ጸሎትን መጸለይ እንጂ ዜማ አልነበረም ሲል ገድሉ ያረጋግጣል ። (ገድለ ያሬድ) ።

ከዕለታት አንድ ቀን ያሬድ ዜማውን ሲያዜም ለመስማት አጼ ገብረ መስቀል ሕዝቡን ሰብስበው ነበርና ፤ አጼ ገብረመስቀል በዜማው ጣዕም ተመስጦ ጦሩን አዘቅዝቆ ቆሞ ሳለ ፡ የያሬድን እግር ወግቶት ነበር ። ያሬድ ግን የሚያዜመውን ዜማ እስከጨረሰ ድረስ በተመስጦ ስለነበረና ፡ ከታወቀውም በኋላ ሕመሙን ታግሦ በመቻል ንጉሡን ሊያሳስበው አልፈለገም ። ንጉሡ ግን ባየው ጊዜ በጣም ደነገጠና አዘነ ።

ትምህርቱን የሚከታተሉና የሚሰበስቡ የያሬድ ደቀ መዛሙርት ብስድራ መንከራ ሐዊራ ብሔር እስክንድራ የሚባሉ ነበሩ።ቅ. ያሬድ በተሰዓቱ መነኮሳት ትምህርት ተመርቶ መንኖ ሰሜን ወደሚባል ከፍተኛ ተራራ ላይ ወጥቶ በምንኩስና የቀረውን ዘመኑን አሳልፎ አል ። የሞተበትም ቀን ግንቦት 11 ቀን ነው ። (ስንክ. ግንቦት 11 ቀን)

ቅዱሳት መጻሕፍትን ከማንበብና ከመጸለይ በቀር ፣ ዜማ ላልነበራት ኢትዮጵያዊት ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ያሬድ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ዜማን ፈጥሮ በማዘጋጀቱ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባለውለታ አባት ነው ።

ብሔራዊ ታሪኩ እንደሚናገርለት ስማኒያ አንድ መጻሕፍትን የተማረ ሊቅ ነበረና ፡ "ንጉሡ ዳዊት ዘማሪ እንደነበረ ፡ እንዲሁም የመዝሙራንን እቋም በማዘጋጀቱ አሳፍ ፡ ኤዶትም ፡ ቆሬ (ቆሬህ) የተባሉ መዘምራን በዜማ ስልት መዝሙራትን በማዘጋጀት ይዘምሩ እንደነበሩ አስታውሶ ደግሞም" ወንጌላዊው ዮሐንስ በራዕዩ ያያቸው የካህናተ ሰማይ መዝሙርም እንዴት እንደሆነ አስቦ "በመመሰጥ ሥነ ፍጥረትን በመመራመር እንዲሁም" ዜማውን ከወፎች ድምፅ ጋር በማስተያየት እያመዛዘነ ስልቱን በማሻሻል በግዕዝ ቋንቋ በቤተ ክርስቲያን እንዲሠራበት ማዘጋጀቱ ታላቅና ቀዋሚ ነገር ሆኖ ይኖራል 1 ዜና መዋ. 25 ፡ 1 - 31 ራዕ. 4 ፡ 10 ፡ 11 ። ም. 5 ፡ 8 ።

የመጀመሪያዎቹ የዜማ ድርሰቶች የቅዱስ ያሬድ ናቸው ለምሳሌ ዝማሬና መዋሥዕት፣ድጓ፣ጾመድጓ፣ምዕራፍ" የያሬድ ድርሰቶች ናቸው ። ነገር ግን በያሬድ ዜማና በድርሰቶቹ መሠረት በየዘመኑ የተነሡት ሊቃውንት በዜማው ሆነ በቅኔቱ ሥነ ሥርዓትና አባባል አዳዲስ ድርሰትን በመድረክ ሳያክሉበት የቀሩ አይመስልም ። ሆኖም የአሁኑ ሊቃውንት በቅርብ የተደረሱትን ብቻ ፣ አዋልድ ሲሉአቸው ፡ ቀደምትነት ያላቸውን የቅዱስ ያሬድ ድርሰት መሆናቸውን ያረጋግጣሉ ። እንግዲህ ከአሁኖቹ ቀደም ብለው የነበሩት አንዳንድ የአዋልድ ድርሰትን በድጓውና በመሰሎቹ መጻሕፍት አግብተው መገ



www.ethiopianorthodox.org

ኘታቸው ከታወቀ ፡ ከእነዚያ ቀደም ብለው የነበሩት ደግሞ፣ አንዳንዱን የአዋልድ ድርሰት ደርሰው በድጓውሊያገቡበት የሚችሉ እንደነበሩ ማሰብን አይከለክልም ።



ቅዱስ ያሬድ

ደግሞ በዜማ ረገድ መሠረቱ የያሬድ መሆኑ ሲታወቅ፤የቆሜ፣አጫብር ፣ ወንጨረ የቤተ ልሔም እየተባለ እንደየአገሩ በልዩ ልዩ ስልትና ሕግ ሲዜም የሚገኘው ፡ ዱሮ በአንድ መንገድ የተማሩት ሊቃውንት ወደያገራቸው ገብተው ሲራራቁ ፤ በተከታዮቻቸው ሊቃውንት የርክርኩ ይዞታና የትሮሮ ዐመሉ በጊዜ ብዛት እየተለዋወጠ አሁን እስከሚገኝበት ሁናቴ በመድረሱ እንደሆነ ይገመታል ።

ለምሳሌ ፦ ሁልጊዜ በመሻሻል የሚገኘው የቤተልሔም ዜማ አሁን እስከ ቅርብ ጊዜ አሮጌ ቤተልሔምና አዲሱ ቤተ ልሔም በሚል ስልት ተማሪ ሲቸገር አልነበረምን ? በዝማሬ መዋሥዕትም ረገድ "የቀለመ ወርቅና የኮከብ" እየተባለ በመምህራኑ ስም የዜማው ስልትና ጣዕም እንደሚጠራ የታወቀ አይደለምን ?

በቅዳሴ ዜማም "የሰደድኩላና የደብረ ዓባይ" በሚል ልዩነት ዜማው እንደሚታወቅ ግልጽ ነገር ነው ።

ስለዚህ በቅዱስ ያሬድ ዜማና ድርሰት መሠረትነት የየዘመኑ ሊቃውንት እያሻሻሉ ወይም እየጨማመሩ ለተከታዩ ትውልድ አገልግሎት መስጠታቸው ሊካድ የሚገባ አይመስልም ። በጥንታዊ መቅድመ ድጓም በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ብዙ ድርሰት እንደተጨመረበት ተገልጸ ተጽፎአል ። (መቅድመ ድጓ በጣና የሚገኝ) ።

አንዳንድ የውጭ ሊቃውንት "ወረድየ ብሔረ ሮሚ ለቤተ ክርስቲያን ርእክዋ... ወደ ሮሜ ወርጄ ቤተ ክርስቲያንን አየኋት" የሚል ድርሰትን ከያሬድ መጽሐፈ ዜማ ውስጥ በማየታቸው ፣ ያሬድ ወደሮሜ ሄዶ የሮም ቤተ ክርስቲያንን ሁኔታውንም ተመልክቶ የውጭ አገር ሥልጣኔን ቀስም የመጣ ሰው ነው ይላሉ ። ኢትዮጵያ ሊቃውንትም ሃሳቡን የተቀበሉ ጥቂቶች አይደሉም ። ዳሩግን "ወረድየ ብሔረ ሮሜ" የሚለው ቃል ሂርማ ከተባለ መጽሐፍ በመጀመሪያው ምዕራፍ ውስጥ የሚገኝ ነው ። ሂርማ ደግሞ ከመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች አንዱ ሲሆን ፡ ጳውሎስ በሮማ መልእክቱ ሰላምታ የጸፈለት ሰው ሆኖ ተገኝቶአልና ፡ ከቅዱስ ያሬድ በፊት የነበረ ሰው ለመሆኑ አያጠራጥርም ። ሮሜ. 16 ፡ 14 ።

መቼም ቢሆን ቅ. ያሬድ ከማንኛውም ከብሉይም ከሐዲስ ከሊቃውንት እየጠቀሰ ለዜማው ድርሰትን የሚያዘጋጅ መሆኑ ስለሚታወቅ ፡ እውነተኛ የዚሁ ቃል አመንጭ ማን እንደሆነ ጥናት እስኪወሰድበትና ሌላም መረጃ እስከሚገኝለት ድረስ ፡ ይህ ጥቅስ በመጽሐፈ ዜማ በመገኘቱ ብቻ ቅዱስ ያሬድ ወደሮሜ ሄዶ ነበር" ለማለት ባይቸኩልበት ይሻል ይመስለኛል ። ሂርማ ገጽ 1 ተመልከት ።

በድጓው ውስጥ ያሉትን ድርሰቶች በማጠራቀም የምዕራፉንም ስልት በማሻሻል የተወሰደው እርምጃ አሁን በአጼ ሠርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት ለመሆኑ ፡ ነባር በሆነ በመቅድመ ድጓው መግቢያ ሆኖ ተገልጾአል ። ሰይቀለ ዜማ የተባለው የቆማ ድጓም ይህን ያስረዳል ።

የዜማ ምልክት መዘጋጀት የተጀመረው አዛገር ራጉኤል አዛገር ጌ - በተባሉ ካህናት አማካይነት በአጼ ገላውዴዎስ ዘመን ነው (ታሪክ ነገሥት ተመልከት) ።

## ቅዱስ ያሬድ በትምህርተ መለኮት

ቅዱስ ያሬድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ልዩ በሆነ ጣዕመ ዜማው ያስጌጣት ሲሆን ዜማን በመመሥረት ብቻ የተወሰነ አልነበረም ።

የዜማው ድርሰት ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር የተገናዘበ ሲሆን ከመንፈስ

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል



# ይህን ያውቁ ኖረዋል?

እጅጉ ረታ

ልጁ ለናት-ላባቱ አንድ ነው ። ከላይ ከታች ተከታይ የለውም ። የአሥራ ዘጠኝ ዓመት ጐልማሳ ነው ። አእምሮው ከተነካ ቆይቷል ። ሰውም ሆነ ማናቸውንም ተንቀሳቃሽ ነገር ሲያይ እንዲያው እንደፈጋ ከብት በርግግ-በርግግ ይለዋል ። በትክክል ማሰብ በእርጋታ ማጥናት ስላልሆነለት የዩኒቨርሲቲ ጥናቱን ለማቋረጥ ተገድዷል ። በተወለደበት ፡ እትብቱ በተቀበረበት ሀገር በካናዳ ቶሮንቶ ፣ እሱን ያላየው ፣ ያልመረመረው እክሌ የሚባል የአእምሮ ሕክምና ባለሙያ አይገኝም ። ያልታዘዘለት መድኃኒት የለም ። የኤሌክትሪክ ሾክ ሕክምና በየጊዜው ቢደረግለትም ፡ ለጊዜው ያስታግሰለት እንደሆን ነው እንጂ አስተማማኝና ዘላቂ ለውጥ ሊያሳይ አልቻለም ። በሚደረግለት ሕክምና ሁሉ ምንም ዓይነት መሻሻል ፣ ምንም ዓይነት ለውጥ ሊያመጣ ባለመቻሉ ለመዳን የነበረው ተስፋ ጭራሹን እየመነመነ ተስፋ አስቆርጦ ነበር ። ቀኑን ሙሉ በመኝታ ክፍሉ ውስጥ ተዘግቶበት ይውላል ያድራል ። ከሕመሙና ከስቃዩ የተነሳ ፡ ሰውነቱ ክፉኛ የተጐዳ በመሆኑም ፡ የዚችን ዓለም ብርሃን ማየቱ ከሚያበቃላቸው የሆስፒታሉ ሕመምተኞች መዝገብ ውስጥ አስቀድሞ ስሙ ከተመዘገበ ውሎ አድሯል ።

ታዲያ ያንድ ቅንጣት ልጃቸውን ከጥቅም ውጭ መሆን ወይም የዕድሜ ገመዱ መበጠስ የተቃረበ መሆኑን የተረዱት ወላጆቹ እንደዋዛ ዝም ብሎ ለመመልከት ትዕግሥት ሊኖራቸው አልቻለም ። ሐኪም ነው የተባለውን ሁሉ ማዳረስ ፣ መድኃኒት ነው የተባለውን ሁሉ መሞከር ነበረባቸው ። በየቦታው ሲያጠያይቁም በመጨረሻ በኒውዮርክ ሲቲ ግሬስ-እስኬር ሆስፒታል ውስጥ በዶክተረ አለን ኰት የሚመራ የአእምሮ ሕመምተኞችን ጾም በማስጾም ተፈላጊውን ውጤት የሚያመጣ ሕክምና የሚካሄድ መሆኑን ወላጆች እንደሰሙ ፣ ውለው-ሳያድሩ ከካናዳ ልጃቸውን በአየር አሳፍረው ኒውዮርክ ሲቲ ግሬስ እስኬር ሆስፒታል ይዘው ደረሱ።

በነገራችን ላይ ዶክተር አለን ኰት በምዕራቡ ዓለም እንደ ሩስያዊው እንደ ዶክተር ዩሪ ኒኰላየቭ ጾም በዘመናዊ ሕክምና ውስጥ ተገቢ ሥፍራ እንዲይዝ ከፍተኛ ጥረት ያደረጉና አሁንም በማድረግ ላይ ከሚገኙት ከፍተኛ ባለሙያዎች እንደ አንጋፋ የሚቆጠሩ ናቸው ።

ታዲያ ይህን ወጣት ወላጆቹ አምጥተው ለኒሁ ዶክተር አለን ያስረክቧቸዋል ። ዶክተሩም ወዲያውኑ የጾም ማጾሙን ፕሮግራም ይዘው ሕክምናውን ይጀምሩታል ። ሥራዬ ብለውም ጾሙ በሰውነቱ ፣ በጤንነቱ ላይ በየጊዜው የሚያመጣውን ለውጥ እስከ መጨረሻው ይከታተሉታል ። ባጭሩ ዕለት-በዕለት ጤንነቱ እየተሻሻለ ፣ ፍርሃቱ እየለቀቀው ከዚያ አስቀድሞ የማያውቀው በራስ የመተማመን መንፈስ በአእምሮ እየሠረፀ ሄደ ልክ የጾሙን ወቅት በጀመረ በአራተኛው ሳምንት ሙሉ ጤንነቱ ተመልሶለት ጤነኛ ሰው ሆኗል ።

ከአራት ዓመትም በኋላ ለኒሁ ዶክተር በጻፈው ደብዳቤ "ዛሬ እንዳለፈው ጊዜ አእምሮዬ አይረበሽም ። መፍራት-መጨነቅ ፡ መሰጋት ፡ የሆነ-ያልሆነው መዘባረቅ የለም ። ይህ ሁሉ ቀደም ቀርቶ ሰው የመሆኔን ምስጢርና (ልኩን) የአእምሮን ክቡርነት የተረዳሁት ሕይወቱንም በትክክለኛው አቅጣጫ ለመምራት የበቃሁት እነሆ አሁን ነው ብሏል ። ይህ ለእርሱም ሆነ ለወላጆቹ ሕይወትን የሚያስመልስ ታላቅ ደስታ መሆኑን ዶክተር አለን ኰት (ፋስቲንግ ዘ. አልቲሜት ዳየት) በተባለው መጽሐፋቸው ጠቅሰውታል ።

በነገራችን ላይ እዚህ ላይ አንድ ነገር እንድጠቅስ ቢፈቀድልኝ? በሐገራችን በደሳሳ ጐጆ ከሚኖረው የኔ-ቢጤ አንስቶ በተደላደለ ኑሮ ሕይወቱን የሚገፋው ሁሉ ካልቸገረው በቀር ጥሬ ቆርጥሞ ፡ ቅጠላ ቅጠል በልቶ መኖር የሚያረካው ከስንት አንድ ይገኝ እንደሆን ቤቱ ይቁጠረው ። ጐመን ቀቅለው ከሚያቀርቡለት ቢጠፋ - ቢጠፋ በአጥንት ውሃ ፈትፍተው እንደ ድመት ካላቀረቡለት የማይዋጥለት ስንቱ ይመስላችኋል ? ገጠሬውን እንተወውና ተምሬአለሁ ፣ አውቃለሁ የሚለው ከተሜማ በእንትን ሲቃጠል ያደረ አንጀቱን ጥዋት በላም ልጅ ካላረሰ ለመንቀሳቀስ ፣ ለመላወስ የሚችል አይመስለም ። ከዚህ ይልቅ እንደ ፍራ-ፍሬ ጭማቂ ፣ እንደ ቅጠላ ቅጠል የመሳሰሉት የምግብ አይነቶች እንኳንስ ለተጐዳ ይቅርና ፣ ለጤናማም ሰውነት ከፍ ያለ ጥቅም የሚያስገኙ መሆናቸውን ተረድተን አሁኑ አበክረን ልንለምዳቸው ይገባል ።

በውነቱ አዘውትረን ሥጋ ፣ ወተትና እንቁላል በምንመገብበት ጊዜ የሚሰማን ለጉሮሮአችን የሚሰጠን ጣዕም ነው እንጂ ፣ በምግብ ማዋሐጃ ፣ በደም ማመላለሻና በመተንፈሻ ሕዋሳቶቻችን ላይ የሚያስከትልብን ድካም ይህ ነው አይባልም ስለዚህ ባጠቃላይ ሰውነታችን በሽታን ለመከላከል ፣ ደዌን ለማጥቃትና ብሎም ለማውደም እንዲችል በጾም ፋታ ልንሰጠው ይገባል ።

በእውነቱ ከጥንት ጀምሮ በዓለም ላይ በልዩ ልዩ የሙያ መስክ የታወቁ ስመ ጥሩ የታሪክ ሰዎች ጾም-ማለት ከማናቸውም የሥጋ ውጤቶች ምግብ መከልከል -በጤንነት ደስተኛ ፣ በዕድሜ ባለፀጋ ወዘተ ለመሆን ዓይነተኛው መሣሪያ መሆኑን አውቀው ፣ መላ ዘመናቸውን ሁሉ ሲፈጽሙት ኑረዋል ። ከእነዚህም ቡድሀ ፣ ፕላቶን ፣ ስክሬትስ ፣ ፕሉታርክ ፣ ዲዩጋንስ ፣ ሚልተን ፣ ጋንዲ ፣ ቶልስቶይ ፣ ቪለር ፣ አይዛክ ኒውተን ፤ ቫልቴር ፣ ሩሶ ፣ ኤዲስንና ሌሎችም ይገኛሉ ። እኛም እስከአሁን ከጥሉላት ምግቦች ለተወሰኑ ወቅቶች የምንከለከለው ሕየንተ ጽድቅ መሆኑ ሲታወቅ ፣ ቤተ ክርስቲያን በምታገዝዘው መሠረት ሰዓቱን ጠብቀን ፣ ጥሬ ጥሬውን ፣ ፍራ ፍሬውንና ቅጠላ ቅጠሉን ብንመገብና ከሚያስከሩ መጠጦች ብን ከለከል በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፎች ገደልን ማለት ነበር ። ስለዚህም በውነቱ አጥብቀን ልናስብበት ይገባል ። ወዲህ መንፈሳዊ ሕይወታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል ፣ ወዲሁም ጤንነታችን ይጠበቃል ማለት ነውና ።



www.ethiopianorthodox.org

# የጥንታዊው ደብረ ሊባኖስ ገዳም ታሪክና ሥርዓተ ሱታፌ

የሰውም ይሁን የቦታ ስም ያለአንዳች ምክንያት ቢጠራ ታሪክ አልባና ትርጉም የለሽ ስለሚሆን ጠሪውንም ሊያሳፍር ይችላል ተጠሪውም ትርጉሙን ካላወቀ ሲጠይቁት መልስ ለመስጠት ስለማይችል እኔን ይሆን ወይስ ሌላውን? በማለት ከመጠራጠር መድረሱ አይቀርም ምክንያቱም ትርጉሙንና ታሪኩን አያውቀውምና ነው

ታሪኩንና ትርጉሙን የሚያውቀው ግን ሲጠሩት አስቀድሞ አቤት ለማለት ይችኩላል በስሙም ደስ ይለዋል ፡፡ ምናልባት የቦታው ስም ከሆነ እንዴት አቤት ይላል? የሚል ጥያቄ ያስከትል ይሆናል ፡፡ መልሱ "በስመ ኃዳሪ ይጼዋዕ ማኅደር" በአዳሪው ስም ማደሪያው ይጠራል የሚል ጥቅስ ስለአለ በቦታው የሚገኙት ሰዎች ተጠሪነቱና ተጠያቂነቱ የእነሱ መሆኑን ስለሚያውቁት እምብዛም ሊያጠያይቅ አይችልም ፡፡

## ወደ ተነሣንበት ርእስ መለስ ብለን የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ለምን ደብረ ሊባኖስ ተባለ? የሚለውን ታሪክ እንመርምር ፡፡

የደብረ ሊባኖስ ገዳም በሰሜናዊ ሸዋ ከአዲስ አበባ 104 ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ ይገኛል ፡፡

በዚህም ገዳም አባ ሊባኖስ የተባሉ መናኝ መነኩሴ ለብዙ ዓመታት ያህል በጾምና በጸሎት በስግደትና በምሕላ ፈጣሪያቸውን ሲለምኑ የኖሩ አባት ከመሆናቸውም ሌላ ብዙ ተማሪዎች ያፈሩ ሐዋርያና መምህር ናቸው ፡፡ አባ ሊባኖስ በዓታቸውን አጽንተው ለመኖር ሲያስቡ ከዛብ ቃታቸው የተነሣ እስከ አሁን ድረስ የጸለይከው ጸሎት ያደረስከው ትሩፋት ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ተሰምቶልሃል፡፡ይህ ቦታ ግን ለሌላ ጻድቅና ሐዋርያ ይሆናል ለአንተ ቦታህ ይህ አይደለም ሆኖም ለድካምህና ለትሩፋትህ ቦታው በአንተ ስም ይጠራል የሚል ቃል በራእይ ስለተነገራቸው ቃሉን በመቀበል ተማሪዎቻቸውን አስከትለው በተለያዩ ክፍላተ ሀገር የሐዋርያነት ተግባራቸውን ሲመሰክሩ ከቆዩ በኋላ በትግራይ ክፍለ ሀገር ስለአረፉ በስማቸው ጽላት ተቀርፆላቸዋል ቤተ ክርስቲያን ታንፃላቸዋል፡፡ ራእዩም ተግባራዊ ሆኖ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም በእርሳቸው ስም ደብረ ሊባኖስ ገዳም እየተባለ ይጠራል፡፡ በተለይ አባ ሊባኖስ ጉልቶ የሚነገርላቸው ታሪክ በየደረሱበት ጸልየው ዐበልማፍለቅ ዕለታዊ ተግባራቸው መሆኑን ከጻድቁ አቡነ ተ ሃይማኖት ደብረ ሊባኖስ ገዳም አባቶች ጠይቀን ባገኘነው መልስ ለመረዳት ችለናል ፡፡

<u>አንባብያን እንዲረዱልን የምንፈልገው ከላይ ስለደብረ ሊባኖስ ገዳም ኃተታ ያቀረብነው ሊባኖስ የጻድቅ ስም መሆኑንና በጻድቁ ስም መጠራቱን ለማሳወቅ እንጂ በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ የምንፈልገው በአጭሩ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የምንኩስናና የሐዋርያነት ተግባር እንዴት እንደነበር ? የሠሯቸውን ትሩፋቶች፣ ከጻድቁ ዕረፍት ወዲህ በገዳማቸው ምንም ሥራ እንደተሠራ መግለጽ፣የገዳሙ መርዓተ ሱታፌና በውስጡ የሚገኙትን ንዋያተ ቅድሳት ጥንታዊነት ማስተዋወቅ የጥንቱንና የአሁኑን ገዳማዊ ኑሮ ማነፃፀር የአስተዳደሩንና አሁን ያለውን ድርጎኛና የመነኮሳቱን ብዛት መተንተን የትምህርቱንና የጸሎቱን ሥነ ሥርዓት መግለጽ ይሆናል ፡፡</u>

## የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የምንኩስናና የሐዋርያነት ተግባር

የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ትውልዳቸውንና ዕድገታቸውን አጉልተን ለመግለጽ ያልፈለግነው በመላው ምእመናን የተለመደ መሆኑን በመገመት ነው ፡፡ ግን ትምህርት ሊሰጠን የሚችለው የምንኩስና ሕይወታቸውና የሐዋርያነት ተግባራቸው ስለሆነ ከአንዳንድ አባቶች ጠይቀን፣ ከጽሑፎች ተመልክተን ያገኘነውን ለአንባብያን እናቀርባለን ፡፡

ሐዋርያው ተክለ ሃይማኖት ከአባታቸው ከፀጋ ዘአብ ከእናታቸው እግዚእ ኀረያ መጋቢት 24 ቀን ተጸንሠው ታኅሣሥ 24 ቀን በ1197 ዓ.ም ተወለዱ፣በጥምቀት ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ስማቸው ፍስሐ ጽዮን እንደነበረ ገድላቸው ይናገራል። አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዕድሜያቸው 22 ዓመት እስከሆን ድረስ በእናት አባታቸው ቤት ሆነው የሕግ አጠባበቅንና የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት የብሉያትንና የሐዲሳትን ትርጓሜ በማጠናቀቅ ከማወቃቸውም በላይ በ15 ዓመታቸው አባ ጌርሎስ ከሚባሉት ጳጳስ የዲቁና ማዕረግ ተቀብለው ቤተ ክርስቲያንን በማገልገልና ልዩ ልዩ የሆኑ በጐ ሥራዎችን ፈጽመዋል ፡፡ ዜና ዕበዩ ለተ/ሃይማኖት ገጽ 15 ተመልከት ገድላቸው እንደሚናገረው በአባት እናታቸው ቤት እንዳሉ ከዕለታት አንድ ቀን ከጓደኞቻቸው ጋር አውሬ ለማደን ሲሄዱ ከዛሬ ጀምሮ የሰውን ነፍስ በትምህርት መጠበቅ እንጂ አራዊትን ማደን አይደለም ስምህም ፍሥሐ ጽዮን መሆኑ ቀርቶ ተክለ ሃይማኖት ይሁን የሚል ቃል ከእግዚአብሔር መልአክ ተነግሯቸዋል ፡፡ ከዚህ በኋላ በወላይታ አውራጃ ባሉበት ጊዜ ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ልትሾም ታቦታትን ቀድስህ ልታከብር ጣዖታትን ልታጠፋ እንደ እኔ ብርሃን ሆነህ የወንጌልን ትምህርት በመላ ኢትዮጵያ አስተምር የሚል ቃል እንደተነገራቸውና በዚሁ አውራጃም መተሉሚ የተባለውን መሪ ከነሕዝቡ ሰማዕትነት በመቀበል መከረው አስተምረው ከአምልኮተ ጣዖት ወደአምልኮተ እግዚአብሔር ከገቢረ ኃጢአት ወደገቢረ ጽድቅ መልሰው አብያተ ክርስቲያናትን አሠርተዋል በዚህም ጊዜ ከመተሉሚ ጋር ብዙ ሰዎች አሳምነው አጥምቀዋል ፡፡ በዚህም ቦታ ለ12 ዓመታት ያህል ወንጌልን በማስተማር የሐዋርያት ተግባራቸውን አስመስክረዋል ፡፡ የሐዋርያት ተግባራቸውን የፈጸሙት ከ1219-1267 ዓመተ ምሀረት ነው ፡፡

## ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሥርዓተ ገዳማትን ለማየት

ሀ/ ቦረና ሳይንት በጸሎተ ሚካኤል ገዳም 10 ዓመት

ለ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም አባ ኢየሱስ ሞ 10 ዓመት

ሐ በትግራይ ክፍለ ሀገር ደብረ ዳሞ ከአቡነ አረጋዊ ገዳም ከአበምኔቱ አባ ዮሐንስ 12 ዓመት አበውን በመረዳትና ልዩ ልዩ ተአምራት በማድረግ ከቆዩ በኋላ ገዳማተ ትግሬንና በኢየሩሳሌም የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መቃብርና ልዩ ልዩ ቅዱሳት መካናትን ጎብኝተዋል ፡፡

ከኢየሩሳሌም ተመልሰው የአቡነ እንጦንስን ሥርዓተ ምንኩስና የአቡነ ጳውሊን ሥርዓተ ብሕትውና ለመፈጸም አሁን መካነ አጽማቸው ወደሆነው ደብረ ሊባኖስ በ1267 ዓ.ም ገብተው ይህን ገዳም መሥርተዋል ፡፡ በዚሁ መጽሐፍ ገጽ 18 ላይ ተጠቅሶ ይገኛል ፡፡ አባታችን ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ይህን ገዳም ከመሠረቱ በኋላ 29 ዓመት እስቦ ከሚባለው ዋሻ በጾምና በጸሎት በቀዊም ሰውነታቸውን ወስነው ዘመናቸውን በመንፈሳዊ ተጋድሎ በሐዋርያነት ተግባር ከፈጸሙ በኋላ ደቀ መዛሙርቶቻቸው የሆኑትን መነኰሳት ሰብስበው ምክርና ትምህርት ሰጥተው በእሳቸው ወንበር ተተክተው አበምኔት ሆነው እንዲያስተዳድሯቸው አቡነ ኤልሳዕን ሾመውላቸው ነሐሴ 24 ቀን 1296 ዓ.ም. ከሚያልፈው ዓለም ወደማያልፈው ዓለም ተሸጋግረዋል ፡፡ ቀብራቸውም በደብረ አስቦ ተፈጽሞአል ፡፡

ይወዷቸውና ይማፀኗቸው የነበሩት መነኮሳትም አዝነውና አልቅሰው አስከሬናቸውን ቀብረው አቡነ ኤልሳዕ አበምኔታቸው ለሦስት ወራት ቆይተው ስለአረፉ በአቡነ ኤልሳዕ ምትክ አቡነ ፊልጶስ ተሹመው አሥራ አንዱን ንቡራን እድ ሹመው 11ም ንቡራን እድ 56ቱን መምህራን በየክፍለ ሀገሩና በየአውራጃው በመሾም አባታቸው አቡነ ተክለሃይማኖት የመሠረቱላቸውን የወንጌል ትምህርት በመላዋ ኢትዮጵያ ለማዳረስ ችለዋል ፡፡

ከዓረፉም በኋላም አጽማቸው በገዳም አስቦና በደብረ ኤላም 57 ዓመታት ቆይቶ አሁን ቤተክርስቲያኑ ካለበት ደብረ ሊባኖስ ገዳም ግንቦት 12ቀን 1353 ዓ.ም በኢትዮጵያ የሚገኙት ልጆቻቸው የሆኑ መነኮሳትና ሕዝበ ክርስቲያን ተሰብስበው ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት ተከብሮ አጽማቸው ወደቤተ ክርስቲያኑ ገብቷል ፡፡

## ከአቡነ ተክለ ሃይማኖትና ከአቡነ ፊልጶስ ጋር የነበሩት መናንያን መነኰሳትና ቅዱሳን ተግባር

ከጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጋር የነበሩት መናንያን መነኰሳትና ቅዱሳን ከዚያም በኋላ በእጨጌ ፊልጶስ እንብርተ እድ የተሾሙትን አህጉረ ስብከታቸውን ዓመቱን ሙሉ በየወሩ ተራ ገብተው በደብረ ሊባኖስ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን አጽምና ታቦተ ማርያም የሚገኙበትን ቤተ ክርስቲያን በማገልገል ለጸሎትና ለማዕጠንት ለቁርባን የሚያስፈልገውን ግልጋሎት ይፈጽሙት ለነበሩት ቦታ ስለሚጠበን ስማቸውን ከመዘርዘር ተቆጥበን በአጠቃላይ ቁጥራቸው ለመግለጽ እንወዳለን ፡፡

ምንም እንኳን አቡነ ተ/ሃይማኖት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወንዶች መነኰሳትና ሴቶች መነካሳይያት ማመንከሳቸው ቢታወቅም በጣም የታወቁትና ለአገልግሎት የተመረጡት 26 ናቸው ፡፡

ከነዚህም ውስጥ እጨጌ ፊልጶስ በአንብሮተ እድ የሾሟቸው 11 አባቶች ሲሆኑ እነዚህም ለእያንዳንዳቸው አህጉረ ስብከት ነበራቸው ይህንንም ሥራ እየሠሩ በደብረ ሊባኖስ ገዳም መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያከናውኑበት የወር ተራ ነበራቸው ፡፡

ሰኔ የአቡነ አኖሬዎስ
ሐምሌ የአቡነ ዜና ማርቆስ
ነሐሴ የአቡነ ዮሴፍ
መስከረም የአቡነ ማትያስ
ጥቅምት የአቡነ መርቆሬዎስ
ኅዳር የአቡነ አድኃኒ
ታኅሣሥ የአቡነ ሳሙኤል
ጥር የአቡነ ኢዮስያስ
የካቲት የአቡነ ታዴዎስ
መጋቢት የአቡነ ቀውስጦስ
ሚያዝያ የአቡነ ገብረ ክርስቶስ

ግንቦት የዕጨጌ ፊልጶስ ነበር እነዚህ ሁሉም አቡነ ተክለ ሃይማኖት በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ያመነኰሷቸው በኵር የተባሉት ናቸው ፡፡

ከእሳቸውም በኋላ ከደቀመዛሙርቶቻቸው ተምረው ትምህርተ ወንጌልን ለማዳረስ የተፋጠኑት መነኰሳት 48 ይሆናሉ ዜና ዕበዩ ለተ ገጽ 24

## የደብረ ሊባኖስ ገዳም ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጊዜ ተሠርቷል ብዙ ጊዜም ፈርሷል

ሀ) በ1399 በእጨጌ ዮሐንስ ከማ ዘመን መነኰሳቱ 7 ዓመት ሙሉ ሠርተው እንዳበቁ አፄ ይስሐቅ ቅዳሴ ቤቱን ለማክበር በመጡ ጊዜ ደስ ብሏቸው የተለያዩ ንዋያተ ቅድሳት ሰጥተዋል ፡፡

ለ) በ1426 ዓ.ም. አፄ ዘርዓ ያዕቆብ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ገዳም ደንብ በየገዳማቱና በየአድባራቱ እንዲሠራበት ወስነዋል ፡፡

ሐ) ግራኝ በተነሣ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኑ ስለ ተቃጠለ ዓፄ ገላውዴዎስ ግራኝን ድል አድርገው ኢትዮጵያን በመንግሥትነት ከያዙ በኋላ የፈረሰውን ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ቅዳሴ ቤቱን ለማክበር መጥተው የደብረ ሊባኖስን ገዳም ሥርዓት አይተው ደስ ስለአላቸው ብዙ ልብስ ተክህናና ልዩ ልዩ የሆነ ሽልማት አድርገው ከመቅደስ እስከውጭው ቅጽር የሚሆን ምንጣፍ ከማበርከታቸውም በላይ በክብረ በዓላቸው ጊዜ ድምፅ የሚሰጡ የተለያዩ መለከቶች አበርክተዋል ፡፡

የአሁኑም ቤተ ክርስቲያን ከሚገኝበት ቦታ ግራኝ ከአቃጠለው ላይ ለመሥራት መሠረቱ ሲቆፈር አንድ ፃህል አንድ ጽዋ ፣ አንድ ዕረፈ መስቀል ፣ አንድ የመፆር መስቀል፣ አንድ የእጅ መስቀል ፣ አንድ መረዋ ተቀብሮ መገኘቱን ከታሪክ መዛግብት ለመረዳት ተችሎአል ፡፡

መ. አፄ ዮሐንስም ለብዙ ዘመናት ያህል ገዳሙ ከገደል በታች ዜጋመል ከሚባለው ወርዶ አሁን ቤተ ክርስቲያኑ ያለበት ጠፍ ሆኖ ሲኖር

በ1870 ዓ.ም ወደዚሁ ቦታ መጥተው መሠረት ጥለው ሥራው በ1876 ዓ.ም. ተሠርቶ ከተፈጸመ በኋላ ለብዙ ዘመናት ሲቀደስበት ኖሯል ፡፡ ለመታሰቢያ የሰጡትም ትልቅ ባለመፆር የወርቅ መስቀል እስከአሁን እንደሚገለገልበት ተረድተናል ፡፡

ሠ. ከአሁን በፊት የነበረውን ቤተ ክርስቲያን ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ለማሠራት ሲያስጀምሩና መሠረቱ ሲጣል አንድ ሳጥን የመላእክትና የቅድስት ማርያም ሥዕል ያለበት ስለተገኘ ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ልጆች ከቅዱሳን አንዱ ይሆናል በማለት 400 እግዚኦታና ምሕላ ከተደረሰበት በኋላ መምህር ወልደ ሚካኤል የሚባሉት ጥንታዊ ሰው የሆኑ የአረጋዊ ገዳም መምህር ቢጠየቁ የአፄ እስከንድር ልጅ ከጐንደር ፍርቃ በር መጥቶ የተቀበረ መሆኑን አስረድተዋል ፡፡

ይህን ለመጥቀስ የፈለግነው የገዳሙን ታላቅነትና የብዙ ሰዎች አጽም በዚህ ቦታ መገኘቱን ለመግለጽ ያህል ነው ፡፡

ዳግማዊ ምኒልክ ያሰሩትም ቤተ ክርስቲያን በ1900ዓ.ም ተፈጽሞ ቅዳሴ ቤቱ በታላቅ ሥነ ሥርዓት መከበሩን በጊዜው የነበሩት አባቶች ተናግረዋል፡፡ ንግሥት ዘውዲቱም ዳግማዊ ምኒልክ አባታቸው ያሠሩት ውስጡ ሳይነጠፍ ቆይቶ ስለነበር በጥርብ ድንጋይ አስነጥፈውና ደጀ ሰላሙን አሠርተው ብዙ አልባሳትና ልዩ ልዩ ንዋያተ ቅድሳት ሰጥተዋል ፡፡

ረ. በ1929 ዓ.ም.ፋሽስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን ወርሮ የደብረ ሊባኖስን ገዳም መነኰሳትና መዘምራን በአካፋና በዶማ ጨፍጭፎ ንዋያተ ቅዱሳቱንና መጻሕፍቱን ዘርፎ ገዳሙን ስለአራቆተው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ 1ኛ መጻሕፍተ ብሉያትን 2ኛ መጻሕፍተ ሐዲሳትን ፣ 3ኛ/ መጻሕፍተ ሊቃውንትን በጠቅላላ ገዳሙ የሚገለገልበትን መጻሕፍትና ንዋየ ቅዱሳት እንዲተካ አድርገዋል ፡፡

በፋሽስት ወረራም ጊዜ ማለት በ1929 ዓ.ም. ግንቦት 12ና 13 ቀን የደብረ ሊባኖስን ገዳም በወረረ ጊዜ ከላይ በተጠቀሰው ቀን ያለቁት አበው መነኰሳትና ካህናት ከአንድ ሺህ በላይ እንደሆኑ በወቅቱ የነበሩት አበው ይናገራሉ ፡፡

<u>በደብረ ሊባኖስ ገዳም ከጻድቁ ተክለ ሃይማኖት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት መንበር የተሾሙት 61 ሲሆን በፀባቴነት ከመቶ አምሳ በላይ እንደተሾሙ ይነገራል</u>

<u>እስከ አሁን ድረስ ያቀረብነው ጽሑፍ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ን ሐዋርያዊ ተግባርና የተከታዮቻቸውን የቤተ ክርስቲያኑን መፍረስና ያሠሯቸውን ሰዎች እንዲሁም በመነኰሳቱና በካህናቱ የደረሰውን ግፍና መከራ ነበር አሁን ግን የገዳሙን ሥርዓተ ሱታፌና በውስጡ የሚገኙትን ንዋየ ቅድሳት ማስተዋወቅ ይሆናል ፡፡</u>

## የገዳሙ ሥርዓተ ሱታፌ

ከአቡነ ፊልጶስ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ በ12 ምርፋቆች ወይም ንቡራን እድ ገዳሙ ሲመራ ይኖራል ይህም የገዳሙን አስተዳዳሪ መጋቢና ጸሐፊ ሳይጨምር ነው ፡፡ እስከ አሁን ድረስ ሲሠራበት መቆየቱን የሚያረጋግጡልን አሁን በሥራ ላይ ያሉትን ለአንባብያን ማቅረብ አስፈላጊ መስሎ ስለታየን ከዚህ ቀጥሎ ስማቸውንና የሥራ ድርሻቸውን ለመግለጽ እንወዳለን ፡፡

1. ፀባቴ ወ አምላከ ወ አማኑኤል የገዳሙ አስተዳደር
2. አሳራጊ አባ ገ ልዑል ክንፈ ሚካኤል የገዳሙ ማኅበር ኃላፊ
3. መጋቢ ወ መስቀል ወ ሥላሴ መጋቢ

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፣ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፣ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።



አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቊጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ

ለትንሣኤ መጽሔት
የምን እንርዳዎ አዘጋጅ

በውነቱ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰውና በቅርብ ጊዜ ውስጥ የመንፈስ ብርሃን በልቦናዬ አብርቶ እኔ በኃጢአት ባህር የሠጠምኩትን ከኃጢአት መንገድ ወደ ጽድቅ መንገድ መልሶኝ ነበር። ነገር ግን የማይታዩት ረቂቃን ባላጋራዎች ማለትም የዚህ ዓለም የጨለማ ገዦች ሠራዊታቸውን በማዝመት በመብል በመጠጥ በማየት በመስማት በዝሙት፣ በሥሥት፣ በፍቅረ ንዋይ፣ በትዕቢት ፣ እኔን ለመጣል በጣም ይዋጉኛል ። (ማቴ 16 ፡ 26) ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል ይላል ።

በእኔ ውስጥ ያለው መንፈስ ደግሞ ወደ ፀረሃ (ወደ ገዳም) ለተጋድሎ ያመለክተኛል ። (ማቴ 16 ፡ 25) ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል ስለ እኔ ነፍሱን የሚያጠፋ ያገኛታል ይላል ደግሞም የዓለም ፍቅር አድሮብኛል በሥጋ ፈቃድና በነፍስ ፈቃድ ውስጥ ነው ያለሁት ስለዚህ በየትኛው ጐዳና እንደምሄድ ቸግሮኛልና አሁን ያለሁት በሥጋ መንገድ ማለትም በማየት በመስማት በመብላት በመጠጣት በልዩ ልዩ ኃጢአት በመበከል ውስጥ ነኝ ከዐሥሩ ሕግጋት አንዲቱ "አታምልክም" ልትሠወርብኝ ነው ታዲያ በጣም እጨነቃለሁ ለጭንቀቱ መፍትሔ እንድትፈልጉልኝ ይህን ጽፌላቸዋለሁ ።

ቄስ አ.ገ.ሥ
ከእንጦጦ አካባቢ

• ቄስ አ.ገ.ሥ. ያቀረቡትን ጥያቄ ተመልክተነዋል ። በእርስዎ ያየነው ችግር በክርስቲያኖች ሁሉ አለ ። በእርስዎ ላይ የዘመቱት ኃጣውዕ በሌሎች አማንያን ላይ ይዘምታሉ ። ግን ብዙዎቹ አማንያን ድል መትተውና አሳፍረው ይመልሱዋቸዋል እንጂ ድል አይሆኑላቸውም ድል የሚነሡአቸው ለጸሎት ለስግደትና ለሥራ ጽሙዳን በመሆን ነው ።

እርስዎም ሰይጣንን ድል ሊያደርጉ የሚችሉት በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው ።

1ኛ/ አዘውትረው ይጸልዩ ፣ ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ ተብሏልና

2ኛ/ ቅዱሳት መጻሕፍትን አዘውትረው ያንብቡ "የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል" 2ጢሞ 3.16/

3ኛ/ በማንኛውም ቦታና ጊዜ ሥራ ፈት አይሁኑ ሥራ ፈትነት የክፉ ሥራ መግቢያ በር ነውና የዲያብሎስን ሽንገላ ተቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ ኤፌ 6 ፡ 10 - 11

4ኛ/ የሚያስጨንቅዎትን ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ይጣሉት በሰይጣንና በክፉ ፍላጐቱ ላይ ድልን ተቀዳጅተው የድል አክሊልን ይቀዳጁ ዘንድ መላ ሕይወትዎን አሳብዎንና ፍላጐትዎን ሁሉ ለኃያሉ አምላክ በእምነት ይስጡ ። 1ኛ ጴጥ 5 ፡ 6 - 11

5ኛ/ ምኞትን ሁሉ ማሸነፍ ይችሉ ዘንድ በመጠን መኖርን ይወቁ ። 1ኛ ተሰ. 5 ፡ 6 - 10

6ኛ/ ሰይጣንንና ፍትወቱን ይቃወሙት እርሱን ከተቃወሙ የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ በልቡናዎ ያድራል ያዕ . 4 ፡ 7 ፡ 9

ስለዚህ በአጠቃላይ በእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ እየተመሩ ክፉ ነገሮችን ለመቋቋም ይሞክሩ ። መቼም ፈተና ለምን መጣብኝ ? ለምንስ ተፈተንኩኝ? ማለት አይቻልም ፈተና ሲመጣ ፈተናን ድል ማድረግ ግን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተማርነው ስለሆነ ፈተናውን ድል ማድረግ ይኖርብናል ። ደግሞም መፈተን ኃጢአት አይደለም ግን በፈተና መውደቅ ኃጢአት ነው ።

ጻድቅ ሰው ሰባት ጊዜ ይወድቃል ሰባት ጊዜም ይነሣል እንደተባለው ፈተና ቢገጥምዎም በገጠመዎ ፈተና ሳይደናገጡ ክፉውን በመልካም ነገር በመቋቋም ከፈተና ለመዳን ይጣጣሩ ።

ምንጊዜም ፈተና አይቀርም ግን የፈተናን መምጣት ተረድቶ መቋቋም ብልህነት ነው ። አንድ ሊቅ "አእዋፍ ከራሳችን በላይ እንዳይበሩ መከልከል አንችልም ። ግን በፀጉራችን ውስጥ ቤት ሲሠሩ ዝም ብለን አንመለከታቸውም" እንዳለው ፈተና ሲመጣ በደካማነት አለመቀበል እንጂ ፈተና ለምን መጣ ማለት አንችልምና በየጊዜው

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



# ዜና አብያተ ክርስቲያናት

## ሸዋ

በሐይቆችና ቡታ ጅራ አውራጃ በሻሸመኔ ደብረ መዊዕ ቅ/ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የማኅበረ ካህናት አምደ ሃይማኖት ካህናትና ወጣቶች ፣ የይርጋ ዓለም የአዋሳ ወጣቶች ከየካቲት 13-17 ድረስ ሰሚናር ተካሂዶ የሰበካ ጉባኤን አቅዋም ለማጠናከርና ንዋየ ቅዱሳትን ለማደራጀት ውሳኔ ማስተላለፋቸው በአባ ያለው ተመስገን ተገልጾልናል ።

## አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ቅዱስ ማኅበር በኢትዮጵያ ለ7ኛ ጊዜ የካቲት 2 ቀን 72 ዓ.ም. በሉተራን ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ስብሰባ አድርጐአል ። በዚህ ዓመታዊ በዓል ላይ የተገኙ ምእመናን ብር 457.96 ለማኅበሩ እርዳታ ያደረጉ መሆናቸው ታውቆአል ።

•••

በምስካዬ ኅዙናን መድኃኔዓለም እስከ አሁን ድረስ የሰበካ ጉባኤ ሳይቋቋም ቆይቶ ነበር ፤ አሁን ግን የቀድሞው የደብሩ አስተዳዳሪ ሊቀ ኅሩያን መርሐ ጽድቅ ገ/ሕይወት ባሳሰቡት መሠረት የካቲት 30 ቀን 1972 ዓ.ም. በቃለ አዋዲው መሠረት ምርጫው ተካሂዶ ሰበካ ጉባኤ ተቋቁሟል ።

## ጋሞ ጎፋ

የጨንቻ መድኃኔዓለም ካህናት ማሰልጠኛ ለ4ኛ ጊዜ ከታኅሣሥ 1 እስከ የካቲት 30 ቀን 1972 ዓ.ም ድረስ በሙያ ማሻሻያ ያሠለጠናቸውን 36 ካህናት የካቲት 30 ቀን 1972 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ የክፍሉ ጳጳስ በተገኙበት አስመርቆአል ።

•••

በጋሞ ጎፋ ሀገረ ስብከት በጨንቻ መድኃኔዓለም በጸሎትና በማርያም ጠበል 28 ሕሙማን ካደረባቸው ከባድ ደዌ የተላቀቁ መሆናቸው በደረሰን ዜና ለማረጋገጥ ተችሏል ።

## ሲዳሞ

በሲዳማ አውራጃ በይርጋ ዓለም ከተማ የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን መንፈሳውያን ወጣቶች የካቲት 20 ቀን 1972 ዓ.ም. በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ዓመታዊ በዓላቸውን አክብረው የዋሉ መሆናቸው በደረሰን ዜና ተረጋግጦአል ።

## ክሬት

የሉተራን ወርልድ ፌዴሬሽን ኰሚሽን ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋር የመጀመሪያውን ስብሰባ አደረገ ።

የሉተራን ወርልድ ፌዴሬሽን ኰሚሽን ወደፊት እ.አ.አ. በ1981 ዓ.ም. የሚደረገውን ስብሰባ በማስመልከት በሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት መካከል ስላለው ባሕልና ሥርዓት ጉዳይ ከመጋቢት 4-10 ቀን 1980 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) በክሬት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ኢኩኑሚካኤል ፓትርያርክ ጋባዥነት ከሰሜን አሜሪካ ከእስያና ከአውሮፓ በአባልነት የተገኙበት በኦርቶዶክስ አካዳሚ ውይይቱ ተካሂዶአል ።

በሉተራንና በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትም ያለው ግንኙነት በጣም አነስተኛ ስለሆነ ሁለቱም ለረጅም ዘመናት ያልተቀራረቡ በመሆናቸው በሁለቱም ወገኖች በኩል ዝግጅት ማስፈለጉን የሉተራን ወርልድ ፌዴሬሽን ዋና ጸሐፊ ዶክተር ካርል ኤች.ማኡ.ጁር ገልጸው ከሌሎችም አብያተ ክርስቲያናቱም ጋር ቢሆን የቅዱስ ቁርባን አፈጻጸም አንድ ዓይነት እንዲሆንና በተጨማሪም ዜናዎችን ለመለዋወጥ እርስ በእርስ ለመግባባትና የተቀራረበ ኅብረትን ለመፍጠር እንደሆነ ከውይይቱ የሚጠበቅ ውጤት መሆን እንዳለበት አስገንዝበዋል ። ሉተራን ወርልድ ፌዴሬሽን ኢንፎርሜሽን ቁጥር 11/80 መጋቢት 19 ቀን 1980 ዓ.ም. እ.ኤ.አ.)

## ቤይሩት

የ33 ዓመት ዕድሜ ያላቸው አባ ቄሺሺያን በሊባኖስ የአርመን ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ሆኑ ። በሐዋርያዊት የአርመን ቤተ ክርስቲያን አንድ ወጣት መነኩሴ ሊቀ ጳጳስ ሲሆኑ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው ። ምርጫው የተፈጸመው የካቲት 23 ቀን 1980 (እ.ኤ.አ) ሲሆን የምርጫው ውድድር የተካሄደው ከ6 ቆሞሳት ጋር ነበር ። አባ ቄሺሺያን በቤይሩት ውስጥ በሚገኘው በአንቲሊያስ የአርመን ሴሚናርና በአሜሪካን ዩኒቨርስቲ እንደዚሁም በጄኔቭ ዓለም ዓቀፍ ተቅዋምና በፎርደም ዩኒቨርስቲ (ኒውዮርክ) ተምረዋል ።

ኢክዩሚኒካል ፕሬስ ሰርቪስ ቁ.8/47ኛ ዓመት መጋቢት 13 ቀን 1980 (እ.ኤ.አ)

# ቅ. ያሬድና .....

ከገጽ ፯ የዞረ

ቅዱስ ባገኘው ልዩ በሆነ በደራሲነት ስጦታው በተዋበ አቀራረብ እያቀነባበረ አምልቶና አስፋቶ የገለጠው ምሥጢረ ቴዎሎጊያው (ትምህርተ መለኮት) ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ የሚታይ ነው ። ይህም ችሎታው በእንዲያው የመጣለት አልነበረም ። በመጽሐፈ ገድሉ እንደተገለጠ ሰማንያ አንዱ መጻሕፍትን በማወቁና ኦርቶዶክሳዊ በሆነ መሠረታዊ አተረጓጐም አራቅቆ በማጠናቀቁ እንደሆነ ይታያል ።

እነሆ መጻሕፍተ ብሉያትንና መጻሕፍተ ሐዲሳትን እንደዚሁም የቤተ ክርስቲያን አዕማድ የነበሩት ቅዱሳን አበው አትናቴዎስና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ባስልዮስና ቄርሎስ ሌሎችም ያጸኑትን ትምህርት በዜማ ድርሰቱ እያቀነባበረ ስለ ትምህርተ መለኮት የገለጠውን ከብዙ በጥቂቱ ለማስረጃ ያህል አቅርበናል።

## 1ኛ/ ስለእግዚአብሔር ህላዌ

"አልቦ አመ ኢሀሎ ወአልቦ አመ ኢሀሎ ።
እግዚአብሔር ያልነበረበት ዘመን አልነበረም የማይኖርበትም ዘመን አይኖርም" (ድጓ)

## 2ኛ/ ስለ ዘለዓለማዊ ህላዌው

"አምላክ ፍጹም በህላዌሁ ፡ ዘሀሎ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ።
አምላክ በሕላዌው (አነዋሩ) ፍጹም ነው ። ዓለም ሳይፈጥር ነበር" (ድጓ)

## 3ኛ/ ስለ ምልዐቱ

"አንተ በሰማይ ወአንተ በምድር አንተ

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዐምድ

## የግንቦት ልደታ

በሃገራችን ልማድ የግንቦት ወር እስ ባበር ከሌሎች ወራቶች ለየት ያ ሁኖ እናገኘዋለን፡፡በግንቦት ወር ጋብቻ አ ይፈጸምም ይኸውም በአፍ እንደሚወ ራው በግንቦት የተፈጸመ ጋብቻ ጽኑ መሠረት አይኖረውም በሚል ሰበብ ሆ ኖ ሌላም ብዙ ይተችበታል ፡፡ ከዚህ ሌላ ከግንቦት አንድ እስከ ግንቦት ሠላሳ ቀን ድረስ በየጉጡ በየደጁ ንፍሮ ይነፈራል፣ ብዙ ድግስ ይደገሳል ፡፡ ይኸውም የሚ ነፈረው ንፍሮና የሚቀርበው ምግብ ሁ ሉ ስለ ቅድስት ማርያም የልደት ክብር መታሰቢያ ነው ፡፡

ስለሆነም በተቻለውና በመሰለው አቅ ሙም በቻለው መንገድ የሚገልጠው ክብር የሚያሳየው ም ፍቅር የሚያደር ገውም መታሰቢያ መሆኑን አንዳንድ ሰዎችን አነጋግረን ገልጸውልናል ፡፡

በሌላ በኩል ግን ከግንቦት አንድ ቀን እስከ ግንቦት መጨረሻ የአድባር እያሉ በየግቢው በየመንገዱ ዳር ይደግሳሉ የሚ ታረደውም በግ መልክ ተመርጦ ለአድ ባር ያርዳሉ ይበላሉ ይጠጣሉ ለግቢአቸ ው አድባር ወይም ለመንደራቸው አድ ባር ይሳላሉ ከሚበሉትና ከሚጠጡት ም በመጀመሪያ ቀንሰው አድባራቸው እንድትበላ ይበትናሉ ይረጫሉ ያስቀ ምጡለታልም፡፡ይህ እንግዲህ በአገር ቤ ት ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማም ጭምር የሚፈጸም ድርጊት ነው ፡፡በበ ለጠ ለመረዳት ያመችን ዘንድ ስለ ግን ቦት ልደታ አንዳንድ ሰዎች የሰጡን አስ ተያየት እነሆ ፡፡

ወ/ሮ አበበች፦ ለግንቦት ልደት የአካባ ቢያችን ሰዎች አዋጥተን ጠላ እንጠምቃ ለን ከእህል ዘር በሙሉ አዋጥተን ንፍሮ እናነፍራለን ቡና እናፈላለን እነባበሮ /ቂጣ በቅቤ አፍሌኝ /እናዘጋጃለን እን ደ አቅማችን አዋጥተን እናርዳለን እን በላለን እንጠጣለን ሽማግሌዎች ይመር ቃሉ ይህ ሁሉ የሚደረገው ግን በእመቤ ታችን ስም እንጂ ሌላ አናመልክም ከ በላነው የተረፈ ካለም እቤታችን ከድነ ን እናስቀምጣለን የእረፍት ቀን ከሆነ ቀንም ቢሆን ተሰብስበን እንበላዋለን ሥራ ቀን ከሆነ ደግሞ ማታ እንጨር ሰዋለን በዚያን ጊዜ አንዳንዶቹ በማር ያም ስም ለሚቀጥለው አመት ስለት ይ ሳላሉ ፡፡ ሲሉ ተናግረዋል ፡፡

ወ/ሮ አቻሜ፦ ለግንቦት ልደታ ጠላ እ ንጠምቃለን ድፎ ዳቦ እንጋግራለን ቂ ጣ በቅቤ እናዘጋጃለን የተሟላለት ቀይ በግ /ጥቁር ቡሃ በግ/ ያርዳል እኛም እና ርዳለን አንድ ዛፍ ሥር ተሰብስበን ንፍ ሮ እናነፍርና በየተራ እየደገስን ከነ ቤተሰቦቻችን እንበላለን እኛ ከመቅመ ሳችን በፊት ግን ሪሚጦ ይዘጋጃል ከተ ልባው ከኑጉ ከቂጣው ከቆሎው ዘግነን በአንድ እቃ አጠራቅመን እጣን አጨሰ ን ከቡናውም ከጠላውም እንደዚሁ አድ ርገን ወደ ጓሮ ሄደን ለአድባሯ አስቀም ጠንላትእንመጣናእንበላለንእንጠጣለን ይህምለልጅለከብት ጤናይሰጣልስለሚ ባል ነው ፡፡ በልተን ከተረፈንም ትራፊ ው ከቤት አይገባም እዚያው እውጭ ነው የሚያድረው ፣ እስካለቀ ድረስም እየተሰበሰብን እንበላለን እንደዚሁም በዚሁ ወር ውስጥ የጉንፋን መድኃኒት ነውየምንለውሌላደግሞራሂሎየሚ ባል በአል አለ ፡፡ ይኸም እንጨቱንም የጥሬ እህሉንም የቂጣ ዱቄትም ከየቤ ታችን አዋጥተን እዛፍ ሥር ሆነን ሥራ ውን እጅ በእጅ እንሰራና ሕጻን ሽማግ ሌ ፣ ወጣት ፣ አሮጊት ተሰብስበን እንበ ላና ወደ መጨረሻ ሲደረስ የተሰበሰበ ው ሁሉ በአንድነት በግራ እጃችን ከን ፍሮው ዘግነን ራሂሎ ነይ ቶሎ ቶሎ'' እያልን በመጓዝ እየጨፈርን እየዘለል ን ገደል አፋፍ ላይ ስንደርስ የአንድ ሰ ው ስም በአንድነት ጠርተን ተቀበለኝ በማለት የዘገንነውን በትነን አንድሰው ወደ ኋላ ሳይቀር ወደኋላም ዘወር ሳይል እየሮጥን ወደ ቤታችን እንመለሳለን ይ ህም ጉንፋኑን ሸኝተን መምጣታችን ስ ለሆነ እኛ ጋ የነበረው ጉንፋን ወደሌላ ው አካባቢ ገባ ማለት ነው ፡፡

ይህ ካልተደረገ ግን በአካባቢው ያሉ ት ባልቴቶች ራእይ አየን ብለው ይነግ ሩናል ይህም ጊዜውን ያሳለፍን እንደሆነ ምነው ዝም አላችሁ ብለው ይቀሰቅሱ ናል ማለቱ ያስታውሱናል እኛም የተለ መደውን እናደርጋለን ብለዋል ፡፡

አቶ ከበደ፦ እንኳን ባመቷ ልደታ በየ ወሩ በልደታ ገንዘብ ብሞት አላጣም በ ተቻለ መጠን እስከጠግብ መብላት እ ፈልጋለሁ ፣ ፍስክ ከሆነ በተለይ የግን ቦት ልደታ ቡሃ በግ አርዳለሁ ካልቻል ኩ ቀይ ዶሮ አርዳለሁ በተቻለ መጠን ም ተደስቸ እንድውል እሞክራለሁ በዚ ሁ ቀን እቤቴ ቡና ተፈልቶ ቆሎ ተቆል ቶ ቂጣ ተጋግሮ ቁጠማ ተ ጐዝጉዞ ከቤ ተሰቦቼ ጋር ተደስቸ እውላለሁ ይህ እ ንግዲህ ሁል ጊዜ በልደታ ሲሆን የግን ቦት ልደታ ግን ዋናዋ ስለሆነች እመን ደራችን የተዋጣውን ሴቶቹ ይሠራሉ እኛም አረቄውን ጠጁን እንገዛለን እየ ተደሰቱ ማምሸት ነው፡፡የእኛ መንደር አ ድባርደግሞሰሚናትልጅቢታመም ለ አድባራችን ከተሳልን ይድናል በጠቅ ላላ አድባራችን በጣም ጥሩ ስለት አድ ራሽ ናት ብለዋል ፡፡

ወ/ሮ ማሚቴ፦ የግንቦት ልደታ ሁሉም እንደሚያደርገው አዋጥተን እንጠምቃ ለን ከዚያ ንፍሮውን ቂጣውን ቅቤም ሆነ ዘይት ሁሉንም እናዋጣና አድባራ ችን ሥር አዘጋጅተን እንመገባለን ፣ጥ ቅሙ ግን አድባራችን ወይ ብላ ሰሚ ስ ለሆነች ለእርሷ ግብር እንገብራለን ልጆ ቻችን ጉንፋን ቢይዛቸው ለአድባራች ን ቡና አፍልተን ቆሎ ቆልተን ቂጣ ጋ ግረን የመጀመሪያውን ስኒ ለአድባሪቱ ድፋት አድርገን ብንለምናት ሳትጨክ ን በማግስቱ ሻል ብሏቸው ያድራሉ አ ድባራችን ሰሚ እንዳለው እናት ስለሆ ነች ያ ሁሉ ስለት ለግንቦት ድግስ በድ ግስ ይሆናል ብለዋል ፡፡



እዚህ ላይ አንባብያን እኛም የግን ቦት ልደታ እመቤታችን የተወለደችበ ት ቀን ነው እርስዎስ ይህንን በዓል ያው ቁታል ወይ? ብለን ወ/ሮ ማሚቴን ጠይ ቀናቸው ነበር እርሳቸው ግን ሲመልሱ እኔስ የአድባራችን ግብር መክፈያ ቀን መሆኑን እንጂ ማርያምስ መወለዷንእል ልሰማሁም ይልቁንስ ይህች አድባራች ን ሲቸግረን የምናዋያት በሆድ ያለ አዋ ቂ መሆንዋን ነው የምናውቀው ሲሉ መልስ ሰጥተውናል ፡፡

እንግዲህ በግንቦት ልደታ ንፍሮ ከ ውጭ በመዋጮ የሚነፈረው ቂጣ በቅቤና በርበሬ የሚቀባው ደም የሚፈ ሰው ስብ የሚጤሰው በአጉል ልማድ እንደ ባህልና ሥርዓት ሆኖ ስለተለመደ ለአድባር ግብር ለመክፈል እንጂ ለቅድ ስት ማርያም ክብር ያለመሆኑ ከላይ በ ተገለጸው ለመርዳት እንችላለን ፡፡ እርግጥ የልደታ ንፍሮ እየተባለ ትንሹ ትልቁ ወንድ ሴቱ ሳይለያዩ ሁሉ ም በትክክል መሰብሰባቸው የማኅበራ ዊ ኑሮ የስምምነት የመልካም ኑሮ ወ ይም ጉርብትና ምልክት ነው ይህም በቅ ድስት ማርያም ስም የሚፈጸም መንፈ ሳዊ ዝክር ሆኖ ስመ እግዚአብሔርን በ መጥራት ቢበሉት ቢጠጡት በዓሉንም በማሻሻል እዛፍ መር መሆኑ ቀርቶ በየ ቤቱ ቢዘክሩ መልካም ነበር፡፡ በእውነት ከተመራመርን የመጀመሪያዎቹ ጀማሪ ዎች ለጥሩ ነገር እንደነበር ከአንዳንድ ታሪክ ተናጋሪዎች ጭምር ለመረዳት ይቻላል ይህም እውጭ የተጀመረበት ምክንያት ይላሉ አንዱ ከሰሜን ክፍለ ሀገር የመጡ አዛውንት በየሰፈሩ ሕዝብ ተሰብስቦ አመብል በፊት ምህላ ይካ ሄዳል ከዚያም ከግንቦት ጀምሮ የዘር ጊዜ ስለሆነ በረከት አውርድ ተብሎ በ መቤታችንና በጌታ ስም ይመረቃል ከ ዚያ ጸሎት ተደርጐ ተበልቶ በጸሎት ይደመደማል እንጂ የሚታረድ እውጭ የሚያድር ነገር የለም ሲሉ አስተያየታ ቸውን ሰጥተውናል ፡፡

ስለዚህ ይህ አጀማመር ለጥሩ ነገር ከነበረ አሁን ከጊዜ ብዛት ከአጉል ል ማዶች ጋር በመዳመር መልኩን ቀይ ሯል ፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም ይህን መ ልኩን የቀየረውን አጉል ልማድ ሕዝ ቧ እንዳይከተል ማስተማሯን አላቋረ ጠችም ይሁን እንጂ ይህንን የግንቦት ልደታን አከባበር ስንመለከት ሕዝቡ ምንም ትምህርት ያገኘ አይመስልም ቢሆንም ሕዝቡ የቤተ ክርስቲያኑን ሕ ግና ሥርዓት በደንብ አድርጐ ማወቅ አለበት እንጂ በስም ክርስቲያን ነኝ እ ያለ በቤተ ክርስቲያናችን በዓል እያሳ በበ የጣኦት ማምለኪያ የአድባር መ ገበሪያ በዓል እንዲያደርግ አንፈልግም፡፡

ብርሃን ተድላ

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ስ ቅዱስን ያሰጡ ነበር ፡፡ ይህ ለምን ቀ ረ?

ተማሪ ቀለሟ ነገደ

ከመጽሔታችሁ ተከታታይ አንደ.

• ተማሪ ቀለሟ ነገደ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ዛሬም አልቀረም በተለያየ መን ገድ ይሰጣል እርግጥ መንፈስ ቅዱስ ሥ ራ ሲያሠራና ኃይል ሲያደርግ እንጂ ሲ ሰጥ አይታይም ፡፡ ስለአንብሮተ አድም እጅ መጫን ጉዳይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚከተለው ክፍል ተመል ከቸ የሐዋ. 8.17 9፣17 1 ጢሞ 4 ፡ 14 ፡ 2ጢሞ 1.6 ይሁን እንጂ እጅ መጫን ለሁሉና በማንኛውም ጊዜ ስለ ማይሆንጥንቃቄማድረግእንደሚገባጳ ውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠውን ምክር ማስተዋሉ ይጠቅማል 1 ጢሞ 5.22 ፡፡

## ቅዱስ ያሬድና ትምህርቱ

ከገጽ ፲፫ የዞረ

በባሕር ወአንተ በቀላያት .... እኮ ንህነ ዘንበብነ ዘንተ አላ አንተ ትቤ'' አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክ ዘመልዕ ልተ ኩሉ ሰማያት ወአነ ህልው ውስተ ኩሉ መካን .... ፡፡

አንተ በሰማይ አለህ ፡ በምድርም አለህ ፡ በባሕር አለህ በቀላያትም (ጥል ቆች) አለህ ... ይህንም የተናገርን እኛ አይደለንም አንተ ራስህ ''ከሰማያት ሁሉ በላይ ያለሁ በዐለም ሁሉ የምኖር እግዚ አብሔር አምላክ ነኝ ብለህ ተናገርህ እንጂ (ምዕራፍ) በማለት ይገልጥና ከነ ቢያት መጻሕፍት ጋር እያገናዘበ ምሥ ጢሩን ያብራራል ፡፡

### 4ኛ/ ስለ ከሃሊነቱ

''አይጽሕቅ ዘይመክሮ
ወኢየኀሥሥ ዘይረድኦ
አልቦቱ ጥንት ወኢተፍጻሜት
ኢየኀልቅ መንግሥቱ
ወአልቦ ዘይክል መዊዐ ኃይሉ ፡፡
እግዚአብሔር መካሪ አይሻም
ረዳትም አይፈልግም ፡
ጥንትና ፍጻሜ የለውም
ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም
ኃይሉን ለማሸነፍ የሚቻለው የለም ፡፡

### 5ኛ/ ስለ ረቂቅነቱና ጥበቡ

እግዚኦ ዘኮሎ ትሬኢ ወተአምር እምር ኑቅ
ወለከሰ አልቦ ዘይሬእየከ
ወአልቦ ዘየአምር ኃይለጥበብከ
ግሩም ግብርከ ወዐቢይ ኃይልከ
ወመንክር ሰብሐቲከ ......
ሁሉን የምታይና የምታውቅ አምላክ ነህ ፡
ግን አንተን የሚያይህ የለም ፡፡
የጥበብህንም ኃይል የሚያውቅ የለም ፡፡
ሥራህ ግሩም ነው ኃይልህ ታላቅ ነው
ክብርህ ድንቅ ነው...'' (ድጓ) በማለት የእግዚአብሔርን ረቂቅነትና ጥበብ በአ ንክሮ ይገልጣል ፡፡

### 6ኛ/ ስለ ቅድስት ሥላሴ

አርያም በሚባለው ድርሰቱ ፦

''ሃሌ ሉያ ለአብ ፡ ሃሌ ሉያ ለወልድ ፡ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ሥላሴ ዋሕድ ...... እብን አመስግኑ ወልድን አመስ ግኑ መንፈስ ቅዱስን አመስግኑ አንድ ነት በሦስትነት ሦስትነት በአንድነት አለ ... ብሎ ትምህርተ ሥላሴን በረቀቀ ሥረይ (ተርሚኖሎጂ) አስተምሮአል ፡፡ (ምዕራፍ) ሥላሴ ዋሕድ'' የሚለው የቅዱስ ያሬድ ተርምኖሎጂ ትሪኒቲ ከሚለው ካላቲን ቃል ጋር ኅብረት አለው ምክንያቱም ትሪ ሦስትነት ኒቲ

ወደ ገጽ ፲፯ የዞረል



www.ethiopianorthodox.org

# የሃይማኖት ዐምድ

«ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፡ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፡፫) ።

## የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ፤

ካለፈው የቀጠለ

"እርሱ (ክርስቶስ) በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል።" (ማቴ. 3፡11) የመጥምቁ ዮሐንስ ተቀዳሚ ምስክርነት ነው ። ይህም ሁለት ዓይነት ትርጉም አለው 1፡- "ፈቃደኞች ብትሆኑና ብታምኑ በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል እምቢ ብትሉ ግን በገሃነም እሳት ያጠምቃችኋል ወይም 2፡- በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት ያጠምቃችኋል ማለት ነው" ካሉ በኋላ ጥንታውያኑ የትርጉም ሊቃውንቶቻችን መልእክቱን በማመሥጠር ሲተነትኑት የሚከተለውን ፍሬ ሐሳብ ያቀርባሉ፡-

"መንፈስ ቅዱስን እሳት ብሎ የሠየመበት ምክንያት አለው ፤ ይኸውም እሳት በሁሉም ነገር ውስጥ ምሉዕ (የተሞላ) ሆኖ ሣለ ቡላድ ካልመቱ አይገለጥም።ለምሳሌ ክብሪት ካልተጫረ፣ዕንጨት ካልተፋጨ ፡ ድንጋይ ከድንጋይ ካልተጋጨ በቀር የእሳት መኖር ወይም ብልጭታው አይታይም። መንፈስ ቅዱስም ለአማኙ ኃይልን በመስጠት ቋንቋ ሲያናግር ፣ ምሥጢር ሲያስተረጉም ፤ ታምራት ሲያሠራ በተግባር ይታያል እንጂ በአካል አይታይም ።

እሳት ደግሞ ከቡላድ ሲወጣ ቀስበቀስ በመጠን ነው እንጂ በአንድ ጊዜ ቦግ ብሎ አይታይም በመጠን ይጀምርና ግን እየሰፋ እያደገ ይሄዳል የመንፈስ ቅዱስም ስጦታ በጥቂት ይጀምራል ።

የመንፈስ ቅዱስ ሀብት በውሃ ጥምቀት ሲሰጥ በመጠን ይሆንና ዘግየት ብሎ ቀስ በቀስ በሚሠራ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር እየዳበረ ይመጣል ።

እሳት ጣዕምና መዓዛ ይሰጣል መንፈስ ቅዱስም ጣዕመ ጸጋን መዓዛ ጸጋን ይሰጣል፣እሳት በመጠን ቢሞቁት ለሕይወት ይጠቅማል፣ከመጠን አልፈው ቢሞቁት ግን የመቃጠል አደጋ ያደርሳል ። መንፈስ ቅዱስም ለምእመናን ሙቀተ ጸጋን የሚሰጥ ሲሆን ለሚክዱት ግን እሳት በላዒ ነው ።

እሳትን ውሃ ካልከለከለው ጋራ ተራራ ካልጋረደው በቀር ሁሉን ለማጥፋት ይቻለዋል ። መንፈስ ቅዱስንም መሐሪነቱ ቸርነቱ የፍቅሩም ምልዓት ስፋት ካልገታው በቀር ሁሉን መደምሰስ እንደሚችል ተጽፎአል ።

እሳት ጹሩን ጫካውን ይገልጣል ፡ መንፈስ ቅዱስም ለአማኞች ምሥጢርን ይገልጣል ። እሳት ማዕድናትን ያጠራል ፡ መንፈስ ቅዱስም የአማኞችን ሕይወት ከኃጢአት ዝገት ያጠራል ያነፃል ። እሳት ሲቀጣጠል ከአንዲት ትንሽ የሻማ መብራት ዕልፍ አዕላፍ ሻማ በማቀጣጠል ቢያበሩ ተከፍሎ እንደማያልቅ የመንፈስ ቅዱስም ስጦታ እንዲሁ ተከፍሎ ሳያልቅ እስከምጽአተ ክርስቶስ ሲናኝ የሚኖር መሆኑን ያመለክታል ።

ሸክላ ሠሪ ሸክላዋን ሠርታ ከተኮሰችው በኋላ ብልሽት ያገኘችበት እንደሆን እንደገና ከስክሳ በውሃ ለውሳ ትሠራና በእሳት ተኩሳ ታድሰዋለች ። በኃጢአት የወደቀ ክርስቲያንም በንስሐ ወደ ክርስቶስ ሲመለስ በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት ተፈትኖ ተሐድሶን ያገኛል ። (ይታደሳል)

ይህ እንግዲህ ሊቃውንት የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በመተንተን ምሥጢሩን ለማስረዳት የሞከሩበት ትርጉም ስለሆነ በትርጉም ላይ ትርጉም መጨመር ሳያስፈልግ መልእክቱን በማጤን እያንዳንዱ አማኝ የራሱን ሕይወት በመመርመር በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት መፈተን አለመፈተኑን ሊገነዘብበት የሚችል መስታወት ያቀረብን ይመስለኛል ።

ስለዚህ ይህን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለማግኘት ማለትም በርሱ እሳትነት ለመታደስ የእያንዳንዱ አማኝ ጸሎት "ቅዱስ መንፈስህን ከእኔ አታርቅብኝ የቀናውንም መንፈስ በልቤ አድስ በጎ ፈቃድ ባለው መንፈስ ደግፈኝ" የሚል ቢሆን መልካም ነው ። (መዝ. 50 ቁ 1፡12)

ቄ. መክብብ አጥናው

## የጥንታዊው ደብረ ሊባኖስ

ከገጽ ፱ የዞረ

4. ቄሰ ገበዝ መጋቢ ገብረ መድኅን ባሣዝን የቤተ ክርስቲያን ገበዝ
5. ቄሰ ገበዝ አባ ሠይፈ ሚካኤል ኃ.ማርያም የገዳሙ ምርፋቅ አባል
6. አባ ሣህሉ ባዩ የገዳሙ » »
7. መጋቢ ካሣ ላቀው » » »
8. አባ በላይ ወ አረጋዊ » » »
9. አባ ወልደ መስቀል ገ ሥላሴ » » »
10. መምህር ወልደ መልአክ ኃይሉ » » »
11. አባ ወልደ ገቢርኤል መለሰ » » »
12. ሊቀ ዲያቆን አባ ወልደ በየነ » » »
13. አባ ገ/ሥላሴ ታመኑት » » »
14. አባ ዘመደ ጊዮርጊስ ወ ሚካኤል » » »
15. ዓቢይ ወልደ መስቀል የገዳሙ አስተዳዳሪ ጸሐፊ

ከዚህ በላይ ስማቸው በዝርዝር የተመለከተው ስለገዳሙ አስተዳደር ተሰብስበው ተወያይተው ውሳኔ የሚያስተላልፉ ናቸው ። ነገር ግን በሥፍራው ተገኝተን ስለገዳሙ አስተዳደርና ሥርዓተ ሱታፌ በጠየቅንበት ወቅት የነበሩትን ሰዎች ለመጥቀስ ያህል በማኅበሩ ተመርጠው የመጡት አባላት ፡-

ሀ ፀባቴ ኃይለ ጊዮርጊስ ወ/ሰማዕት — አባል
ለ/ መጋቢ ጥበቡ ወርቅነህ — »
ሐ/ መጋቢ ታደሰ ወ/ትንሣኤ — »
መ አባ ሥዩም ውብሸት — »
ሠ/ አባ ከሃሊ በየነ — »
ረ - አባ የማነ እንግዳ — አባል
ሰ - አባ መንክር ተክለ ሃይማኖት"
ሸ - ገ/ ጻድቅ ኃይሉ የገዳሙ ገምጃ ቤት ጸሐፊ ነበሩ ። የገዳሙ ሥርዓተ ሱታፌ የሚመራው ከጥንት ጀምሮ በአስተዳዳሪውና በመጋቢው እንዲሁም በ12 ምርፋቆች ነው ።

ፀባቴው በኃትርያርኩ ወይም በእጨጌው ይሾም እንጂ መጋቢውና 12 ምርፍቆች የሚመረጡት በማኅበሩ እንደሆነ ሚያዝያ 10 ቀን 1918 ዓ.ም. የወጣው የደብረ ሊባኖስ ገዳም ደንብ ያስረዳል ።

እነዚህም ከመመረጣቸው በፊት ማኅበሩ ብቃታቸውንና ለገዳሙ የሰጡትን ግልጋሎት በማመዛዘን በማኅበሩ ዘንድ ተወዳጅነታቸውም ያህል እንደሆነ በመገምገም ፣ ከራሳቸው ይልቅ የማኅበሩን መሻሻል የሚፈልጉ መሆናቸውን በማረጋገጥ መምረጥ እንደሚገባ ደንቡ ይጠቁማል ።

እንዲያውም ከላይ የጠቀስነው ደንብ

ሀ - ስለ ደወል ሥርዓት
ለ - ስለ መስቀሉ ቤት
ሐ - ስለጸሎተ ማኅበር
መ - ስለ ሰዓታት
ሠ - ስለ መቁነን
ረ - ስለ እንግዳ አቀባበል
ሰ - ስለ ማኅበሩ ልክና ቁጥር
ሸ - ስለ ሥራ መሥራት
ቀ - ስለ ምርፋቆች ያሠፈረውን ጽሑፍ በዝርዝር ለማቅረብ እንወዳለን ።

## የደወል ሥርዓት

ደወል ብቻ ሲመታ የሚቀድሱና የሚያስቀድሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሔዱ ደወልና ከበሮ በአንድ ላይ ሲመታ ለፍትሐትና ለማኅሌት ባለ ሥራዎች ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሔዱ መጥቀዕ ብቻ ሲመታ በገዳሙ ያለው ሰው ሁሉ የየጊዜያቱን ጸሎት ያድርስ መጥቅዕና ነጋሪት ሲመታ ማኅበር የሆነ ወደምርፋቁ ለጸሎተ ማኅበር ይሰበሰብ የቅዳሴው እንደ መጽሐፉ ሥርዓት የማኅሌቱ እንደአጋፋሪው ትእዛዝ የጸሎተ ማኅበሩ እንደመጋቢው ትእዛዝ የሚደወል መጋቢው ሁለት ረዳት ጨምሮ አንድ ሊቀ ትጉሃን በደወል በኩል የሚያገለግሉት በሊቀ ትጉሃን ይላል ።

## የመስቀል ቤት

በሦስት ታላላቅ በዓላት ስለመስቀሉ ክቡር መነኮሳት ሁሉ በዋዜማው በመስቀል ቤት መስቀሉን ይዘው ወደ ትልቁ ቤተ ክርስቲያን ይሔዳሉ ። በዚህም ጊዜ የሚቀድሱት የተመረጡት መናንያን መሆናቸውን ያስረዳል ።

## ጸሎተ ማኅበር

ጸሎተ ማኅበር የሚደረግበት ሰዓት ማኅበሩ በደወል እየተሰበሰቡ ጸሎተ ማኅበር እንዲያደርሱ ይታዘዛሉ ጸሎቱም ከሁለተኛ ደወል በኋላ ይጀምራል ።

ከታመመና ወይም ሽምግሎ ከደከመ በቀር ለጸሎተ ማኅበር ያልመጣ ሰው በመጀመሪያ በማኅበሩ ፊት ቆሞ ይወቀሳል ከፍ ያለ ስግደት ይሰግዳል በሁለተኛው የአንድ ቀን ድርጎውን ይከለከላል በሦስተኛው ቀን ወደንስሐ ቤት ገብቶ ከንስሐው እንዲመለስ ይመከራል ። የማይመለስ ከሆነ ግን ከማኅበሩ ይለያል ሲል ይገልጻል ።

## ሰዓታት

ለሰዓታት ወይም ለጉባኤ ጸሎት በመስቀል ቤት ደወል በተደወለ ጊዜ ከሽማግሌዎችና ከበሽተኞች በቀር ከ12 አባቶች (ምርፋቆች) የሚችሉት ወደመስቀል ቤት እየሔዱ ሰዓታት ይቆማሉ ሌላው ማኅበር ግን በተራው ያልታዘዘ በፈቃዱ ከታላቁ ቤተ ክርስቲያን ይቆማል በማለት ያወሳል ።

## መቁነን

የደብረ ሊባኖስ ፀባቴውና መጋቢው ለ12 አባቶች እስከ አሁን የተለመደውን መቁነን በዝቶም እንዳይተርፍ አነሱም ማኅበሩ እንዳይጐዳ የመቁነኑን ልክ ይጠብቃሉ ። ከማኅበሩ ጋር አንድነት ሆኖ ድርጐ የሚበላ ሰው ንብረት የሌለው ፣ ንብረት ያለው ሰው አይብላ ድርጐ ልብላ ሲል ንብረቱን ለማኅበሩ ያግባ ። ይህም ለልጆቹና ለዘመዶቹ ከሰጠው በቀር ነው ሲል ይገልጻል ።

## ስለእንግዳ አቀባበል

በደብረ ሊባኖስ ገዳም ከኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት የሚመጡትን ሊቃውንትና መነኰሳት መጋቢው እየተቀበለ በእንግዶች ማረፊያ ቤት ያስቀምጣል እስከ ስምንት ቀን መስተንግዶውን እንደገዳሙ ሥርዓት እንደማኅበሩ ልክ መቁነን ይልክላቸዋል ከስምንት ቀን በኋላ ግን መቁነን አለመስጠታቸውን ያስታውቃል ።

## ስለ ማኅበሩ ብዛትና ማነስ

ስለ ማኅበሩ መብዛትና ማነስ ፀባቴውና መጋቢው 12 አባቶች ባንድነት ሆነው ከገንዘቡ አቅም የማኅበሩ ቁጥር በዝቶ እንዳይቸግር የመናንያኑም ቁጥር አንሶ ገንዘቡ እንዳይጠራቀም የማይበላውና የሚበላው ተስተካክሎ እንዲዳረስ ያደርጋሉ እንጂ ለቁመተ ሥጋ የሚበቃቸውን ካገኙ ለተድላ ደስታ ያንሰኛል በስምረት እኖራለሁ በአንድነት እፀናለሁ ብሎ ለመጣ መናኒ አትጨምር እኔ ያንሰኛል የሚል መናኒ ለማኅበሩ ጠንቅ ስለሚሆን በመጋቢውና በፀባቴው የመውጣትና የመግባቱ ጉዳይ ሊፈጸም ይችላል ።

## ሥራ ስለ መሥራት

በደብረ ሊባኖስ ገዳም ማኅበር የሚኖሩ ሰዎች በሽተኞችና ሥራ የማይችሉ ካልሆኑ በቀር ወይም በጸሎት ተወስነው ከዘጉት በቀር ለማኅበሩ ጥቅም የሚሆነውን ሥራ በጉልበታቸው እንዲረዱት ከፀባቴውና ከመጋቢው ይታዘዛሉ እንጂ ሥራ ፈት ሆነው እንዲኖሩ አይፈቀድም የደብረ ሊባኖስ ፀባቴውና መጋቢው 12 ምርፋቆች አባቶች ተጨምረው በማኅበሩ ስም የተጻፈበትን መዝገብ አቅርበው እንደሚቻላቸው መጠን እያመዛዘኑ ሥራ ፈት ሆነው ገዳማዊውን ኑሮ እንዳይጉዱ ሥራውን እንደሚችለው መጠን ጉልበት ያለው ሰርቶ አልሠራም ቢል ፀባቴውና መጋቢው ከመከሩት በኋላ እንቢ ቢል ማኅበሩ ምክርበት በመጀመሪያ ስግደት ይሰጠዋል እምቢ አልመለስም ካለ ግን ከማኅበሩ ይለያል።

## ስለምርፋቆች

ምርፋቆች የሚባሉት 12 አባቶች እንደሆኑ ገልጸናል ግን ከፀባቴውና ከመጋቢው ጋር የገዳሙን መርዓተ ሱታፌ (መርዓተ ማኅበር) የበላይ ሆነው የሚመሩት እነርሱ መሆናቸውን ጠይቀን ያገኘነውን መልስና ከታሪክ መዛግብት የተገኘውን ለመግለጽ እንፈልጋለን ።

## ከ12 አባቶች መካከል

ሀ - አራቱ መንፈሳዊውን ሥነ ሥርዓት የሚሠሩና የሚቆጣጠሩ

ለ - አራቱ አፈ ጉባኤ ሆነው በማንኛውም በኩል ለሚመጣው ተጠሪ የሚሆኑ

ሐ - አራቱ በቤተ ክርስቲያን በኩል ለአለው አገልግሎት የሚፋጠኑና ትእዛዝ የሚያስተላልፉ ናቸው ይህም ሲባል በተለያየ መንገድ ይሠራሉ ማለት አይደለም።

ሌሊት ሁሉም እንደተቻለው መጠን በቤተ ክርስቲያንም ይሁን በየግል መኖሪያቸው ሲጸልዩ ካደሩ በኋላ ልክ በ12 ሰዓት ሁሉም መስቀል ቤትና የታቦተ ማርያም ጽላት ባለበት ቤተ ክርስቲያን የየግላቸው መጸለያ ቦታ ስላላቸው ልክ 2 ሰዓት እስከሚደርስ በአንድ በዚያው ይጸልያሉ ሁለት ሰዓት ሲደርስ በአንድነት ሆነው "ተፈሥሒ ማርያም" ብለው አስፈላጊውን ሥነ ሥርዓት ከፈጸሙ በኋላ በ3 ሰዓት ምርፋቆች በሚባለው ቤት ከፀባቴውና መጋቢው ጋር ስብሰባ በማድረግ ስለ ገዳሙና ስለማኅበሩ ኑሮ ስለቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ስለአንዳንድ ጉዳዮች በመወያየት እስከስድስት ሰዓት ወይም የቅዳሴው መግቢያ ሰዓት እስከሚደርስ ይቆያሉ ። በዚህም ሰዓት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ

ወደ ገጽ ፰ የዞረል





www.ethiopianorthodox.org

## ሊቃውንቶቻችን

### የአራቱ ጉባኤያት ሊቅ መምህር ፊላታዎስ

በትምህርት በመልካም ጠባይና በማስተማር ታዋቂ የነበሩት ፣ የቅዱስ ጳውሎስንም ፈለግ በመከተል ዓለም በእኔ ዘንድ የሞተች ናት ፣ እኔም በዓለም ዘንድ የምትኩ ነኝ በሚል መንፈስ ሲመሩ የኖሩት መምህር ፊላቴዎስ የትውልድ ሀገራቸው በጎጃም ክፍለ ሀገር በመርጡለማርያም አካባቢ ነው ። የተወለዱትም በ1863 ዓ.ም. ነው ።

### ትምህርታቸው

ገና በሕፃንነት ዕድሜያቸው የንባብ ትምህርት ተምረው ዳዊት ከደገሙና ፀዋትወ ዜማን በየመልኩ ከተማሩ በኋላ ለማናቸውም ዓይነት መንፈሳዊ ትምህርትና ጥልቅ ምርምር ፍቱን የሆነ መክፈቻው የቅኔ ሙያ መሆኑን በእስተማማኝ ሁኔታ ስለተረዱት ወደ ታወቀ የቅኔ ጉባኤ ት/ቤት ገብተው የግእዝንና የቅኔን ትምህርት ተማሩ ።

### በትርጓሜ ብሉያት ት/ቤት

የኢትዮጵያ ሊቃውንትን ዕድሜ በትምህርት ቤቱ ከሚያገባድዱት አንደኛውና በሥርዐተ ትምህርት ይዘቱም አድካሚ የሆነው የ46 መጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜ መሆኑ አያከራክርም የብሉያትን ትርጓሜ ከሊቃውንቱ የሚያጠኑት ደቀ መዛሙርት በመጀመሪያ ንባቡን ቀጥሎም አንድም በሚል የትርጓሜ አወራረድና ቅንብር አማርኛው ሳይለወጥና ቅደም ተከተሉ ሳይፋለስ ነጠላውን ሳይሆን አንድምታውን የምሥጢርና የምርምር ትርጓሜውን ነው ።

በዚህ ዓይነት የትምህርት ሂደት ላይ በቅድሚያ ያተኮሩት ብልሁ መምህር ፊላታዎስ ከላይ እንደተመለከተው የቅኔን ትምህርት ከነአገባቡ አጣርተው ካወቁ በኋላ ከዚያው ከጎጃም ክፍለ ሀገር ወደ ዕላሎ ሄደው በሊቅነታቸው እጅግ ከታወቁት ከመምህር እንግዳ ወማርያም የመጻሕፍቱ ብሉያትን ትርጓሜ ተማሩ ። ይህንኑ ትርጓሜ ከታወቁና ስመ ጥሮች ከሆኑ ሊቃውንት በተደጋጋሚ ለመከታተልና የአንድን ሊቅ ትርጓሜ ከሌላው መምህር የምርምር ስልት ጋር ለማስተያየትና ለማመሳከር በነበራቸው ጽኑ ፍላጎት ቀጥሎ በደብረ ወርቅ ይገኙ ከነበሩት ሊቅ መምህር ሰው አገኘሁ ፣ ከዚያም በኋላ ወደ ግራርማ ቅ ሚካኤል ደብር ሄደው በጣም ስመ ጥሩሊቅ ከነበሩት ከአለቃ ገብረ ኤልያስ የብሉያት ትርጓሜ በማጥናት ዕውቀታቸውን በተከታታይ አጠናክረውና አስመስክረው ለማስተማር የሚያስችል የተሙዋላ ችሎታ አግኝተዋል ።

### ትርጓሜ ሐዲሳት

የመጻሕፍተ ሐዲሳት ንባብና ትርጓሜ ትምህርት እጅግ አድካሚ መሆኑ ቢታወቅም በብሉያት ትርጓሜ የአእምሮ ስልታቸው የተዳመጠ ብሩህ የሆነላቸው መምህር ፊላታዎስ ከተመሰገኑት ሊቅ ከአለቃ ጎሩይ ፈንታ ዘንድ የመጻሕፍት ሐዲሳትን ትርጓሜ ተማሩ ።

### የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኮሳት ትርጓሜ

መምህር ፊላታዎስ በወሎ ክፍለ ሀገር ቦሩ ሜዳ ሄደው በተሙዋላ የትምህርት ይዘታቸው ከታወቁት ሊቅ ከመምህር አካለ ወልድ ሠርፀ ወልድ የመጻሕፍተ ሊቃውንትንና የመጻሕፍተ መነኮሳትን ትርጓሜ በሚገባ አጥንተው የአራቱ ጉባኤያት መምህር ሆኑ ።

### የተፈጥሮ ዝንባሌ

የትርጓሜ መጻሕፍተ ሊቃውንት ትምህርት ለሃይማኖት ትምህርት ፣ የመጻሕፍተ መነኮሳት ዕውቀት ሥጋዊውን ዓለም ወደ ኋላ ትቶ መንፈሳዊውን ዓለም ለመከተል የሚያስችል ስለሆነ መምህር ፊላታዎስ ከላይ በመነሻው እንደታየው ሁሉ ሃይማኖትን ከበጎ ምግባር ጋር አስተባብረው በመያዝ ሐዋርያው ያዕቆብ ሃይማኖት ያለ ምግባር የሞተች ናት ያለውን መመሪያ በሥራ ተረጎሙ ። ትምህርታቸውም በተፈጥሮ ከተሰጣቸው መልካም ጠባይ ጋር ስለተዋሐደ ደገኛ ሰውነታቸው በሁሉ ዘንድ የታወቀ ነው ።

### ፍላቴ ፊላታዎስ

የመምህር ፊላታዎስ አስተማሪ መምህር አካለ ወልድ ፣ ፊላታዎስ የትምህርት ፣ የቀና ሐይማኖትና የእውነተኛ ምግባር ተከታይ መሆናቸውን ለረጂም ጊዜ ከገመገሙ በኋላ ፍላቴ ይባል የነበረውን ስማቸውን ለውጠው ፊላታዎስ ብለው ሰየሙአቸው ። ቃሉ ግሪክ ሲሆን ብዙ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ተጠርተውበታል ። ከእነዚህም የታወቀው ፊላታዎስ ሊቀ ጳጳስ ዘእስክንድርያ ነው ።

### ፊላታዎስ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም

መምህር ፊላቴዎስ በንባብና በትርጓሜ በዓይነ ሕሊና የአዩአቸውን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ዘር ለማዳን ሰው ሁሉና የተአምራትና የትድግና ሥራ የፈጸመባቸውን የተቀደሱ ቦታዎችን በዓይነ ሥጋ አይተው እጅ ለመንሳት በነበራቸው ጽኑዕ ፍላጎት መሠረት ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ሄደው ቅዱሳት መካናትን ጐብኝተው ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል ።

### ፊላታዎስ በትርጉም ሥራ

አባቶች "በቃል ያለ ይረሳል በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል" እንደሚሉት ሁሉ መምህር ፊላታዎስ ከሌሎች የኢትዮጵያ ሊቃውንት ጋር ብሉያትን በአንድምታ ተርጉመው በዘመናዊ ማኅተም ታትሞ ለኢትዮጵያ ሊቃውንትና ምዕመናን እንዲደርስ አቅርበዋል ። መጽሐፉ እስካሁን ድረስ ባይታተምም ለወደፊቱ በማኅተም ተባዝቶ የሚነበብበት ጊዜ በናፍቆት ይጠበቃል ይኸውም ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ ክርስቲያን ታላቅ ውለታ ማድረጋቸውን ያመለክታል ።

መምህር ፊላታዎስ ግፈኛው ፋሽሽት ኢጣልያ ከኢትዮጵያ ከተባረረና ነፃነት ከተመለሰ ወዲህ በዚሁ በዋናው በመናገሻ ከተማ በተቋቋመውና ብዙዎቹን ኢትዮጵያውያንን በትምህርት አሳድገው በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ት ቤት የመጻሕፍተ ብሉያትን ትርጓሜ እንዲያስተምሩ ተደርጎ ብዙዎች ሊቃውንትን በትምህርት ወልደዋል ። ከብሉያት ትርግዋሜ ተማሪዎቻቸው መካከል የዶክተርነት መዐርግ የተቀበሉት ዶክተር አለቃ አየለ ዐለሙ ይገኙባቸው ነበር ።

### የደብር አስተዳዳሪነት

መምህር ፊላታዎስ የዚህ ዓለም ሹመትና ክብር ፈርተው ፈጽሞ የጠሏቸው በሥጋዊው ዓለም ባሉ መንፈሳዊ የሆነው የሰማያዊው ዓለም ፍቅር የሚስባቸው በመሆናቸው በበኩላቸው ፍላጐትና ደጅ ጥናት ሳይኖራቸው የሊቅነት ደረጃቸውና የተሟላ ጠባያቸው ይዘት ተገምቶ በጐጃም ክፍለ ሀገር የመርጡለ ማርያም ደብር መምህርነት ተሰጥቷቸው ሲያስተዳድሩ ቆይተዋል ።

የኢትዮጵያ ሊቃውንትም በበለጠ የሚያስመሰግናቸው ሀሊናቸውን ወደ ትምህርትና ምርምር አሠማርተው በጉባኤ ሊቃውንት ከዋሉና ምሥጢረ መጽሐፍትን ካደላደሉ በኋላ ስለሹመት በደጅ ጥናት በአማላጅ ሹመት ከመካሰስ ይልቅ ጉባኤ ዘርግተው በማስተማር በትምህርት ከአበው ያስቀሩትን ሞያ ለትውልድ ለማስተላለፍ የሚያደርጉት ከፍተኛ ምርጫ ነው ። መምህር ፊላታዎስ መላ ሕይወታቸውን ለትምህርት ለማስተማር ለምርምር መጻሕፍትን ለመተርጐምና ለልዩ ልዩ በጐ ተግባር ቢመድቡትም ይኸንን ሁሉ ተግባር የሚያከናውኑት ቀን ሌሊት ሳይለዩ በብርቱ ሁኔታ የሚያሠቃያቸውን ደዌ በመታገሥና ባለመመረር ነው ፣ እንዲያውም ይኸንኑ ደዌ እንደገድል ቆጥረውት ፈጣሪያቸውን ያመሰግኑበት እንደነበር ይነገራል ።

### ጊዜ ዕረፍት

መምህር ፊላታዎስ በጽኑዕ ሃይማኖታቸው በበጐ ተግባራቸው ከፈጣሪያቸው ዘንድ አንዳንድ ምልክቶች ለማግኘት ችለው ነበርና የዕረፍታቸው ጊዜ እንደተቃረበ ዐውቀው በ1941 ዓ.ም. ወደትውልድ አገራቸው ወደሆነውና በጐጃም ክፍለ ሀገር ወደሚገኘው መርጡለማርያም ሔደው በሰኔ 10 ቀን 1942 ዓ.ም. በተወለዱ በ79 ዓመታቸው አርፈው ከዚያው ተቀበሩ ።

የዕረፍታቸውም ዜና በአዲስ አበባ ከተማ ከተሰማ በኋላ ሐምሌ 3 ቀን 1942 በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት ሊቃውንት ካህናት ደቀመዛሙርቶቻቸውና ወዳጆቻቸው የሆኑ ምእመናን ሁሉ ተሰብስበው ሥርዓተ ፍትሐት ደርሰውላቸዋል ቃላቅ የሆነ የኀዘን መግለጫም ተደርጐላቸዋል ።

አለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ

---

## ቅ. ያሬድና ......

ከገጽ ፲፫ የዞረ

አድነት በተገናኘ ፣ አንድነት በሦስትነት፣ ሦስትነት በአንድነት ማለት ነውና ሥላሴ ዋሕድ ማለትም ሦስትነት በአንድነት አንድነት በሦስትነት ማለት ነው ።

ከዚህም ሌላ ቅዱስ ያሬድ በአጭር ሥርዐተ ሃይማኖት (ክሪድ) ስለ ሥላሴ ዋሕድ እንደሚከተለው ያስተምራል ።

"ነአምን አበ ፈናዊ
ወነአምን ወልደ ተፈናዌ
ወነአምን መንፈስ ቅዱስ ማሕየዌ .....
ፈነዊ አብን እናምናለን
በፈቃዱ የተላከ ወልድን እናምናለን
ሕይወት ሰጭ መንፈስ ቅዱስንም እናምናለን ..... (ድጓ)

### 7ኛ/ የቃለ እግዚአብሔር ወልድ

ወደዚህ ዓለም መምጣትና በተዋሕዶት ሥጋ መገለጥ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ አለመሆኑንና ከጥንት ጀምሮ ትንቢት የተነገረለት ሱባዔ የተቆረጠለት መሆኑን ሲያስረዳ፡-

"ነቢያት ዘሰበኩ ዜናሁ
እሙነ ኮነ ናሁ
ወልድ ተፈነወ እምኀበ አቡሁ

ነቢያት ዜናውን የተናገሩለት እነሆ ተረጋገጠ ፣ ወልድ ከአባቱ ዘንድ በፈቃዱ ተላከ" በማለት አስታውቆአል ። (ድጓ) ከዚህም ሌላ እንጺሖ ሥጋሃ ቅዱሶ ኪያሃ ኅደረ ላዕሌ ሥጋዋን አንጽቶ እርስዋን ቀድሶ ከእርሷ ተዋሐደ ሲል የተናገረው ትምህርት ጥልቅ ምሥጢርን የያዘ ነው ።

### 8ኛ/ ስለ ክርስቶስ ልደት

"...... ዮም ተወልደ እግዚእ ወመድኅን ቤዛ ኩሉ ዓለም...... የዓለም ሁሉ ቤዛ የሆነው ጌታና መድኅን ዛሬ ተወለደ ሲል የዓለም ቤዛነቱን ጌትነቱንና አዳኝነቱን መስክሮአል ። (ድጓ - )

### 9ኛ/ ስለ ጥምቀቱና አስተርእዮቱ

"ክርስቶስ አስተርአየ ውስተ ዓለም
እምድንግል ተወልደ
ከሡተ ኮነ እንዘ ይትኤዘዝ ለአዝማዲሁ
ከዊኖ ሰብአ በዮርዳኖስ ተጠምቀ
ክርስቶስ በዚህ ዓለም ተገለጠ
ከድንግል ተወለደ
ለወገኖቹ እያታዘዘ በግልጥ ታየ
ሠላሳ ዓመት ሲሞላው በዮርዳኖስ ተጠመቀ"

እያለ ስለ ልደቱ አስተርእዮቱና ጥምቀቱ ጥልቅ ምሥጢር ባለው ሁኔታ ምስክርነቱን ይሰጣል ።

### 10ኛ/ ስለ ሕማማቱ

ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕማማትና ለቤዛ ዓለም ስለመሞቱ ከተናገራቸው ክፍሎች ደግሞ የሚከተለውን እናስተውል ።

"ተሰቅለ ወሐመ ዘእንበለ ኃጢአት....
እስመ መለኮቱ ኢሐመ ተሰቅለ እመ እቡስ
ማእከለ ክልኤ ፈያት ።
ወኮርእዎ ርእሰ በኀለት





www.ethiopianorthodox.org

ረገዝዎ ገቦሁ በኩናት ለአምላክ ምሕረት ለንጉሠ ስብሐት ።
ስፍሐ እደዊሁ ቅዱሳተ ዲበ ዕፀ መስቀል ወተቀነወ በቅንዋተ መስቀል ። ከመ ያግእዘነ እምኃጢአት ።
የዑም መስቀል ተሰብሐ
ዓለም ተፀውዐ
እግዚአብሔር ተእኵተ
ወሰብእ ግእዘ
ወሰይጣን ተዐሥረ በኃይለ መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ።

ክርስቶስ ተሰቀለ ኃጢአት ሳይኖርበት በመለኮቱ ኢሐማሚ የሆነ እርሱ በሥጋ መከራ ተቀበለ በሁለት ወንበዴዎች መካከል እንደ ወንጀለኛ ተሰቀለ ራሱን በዘንግ መቱት ። የምሕረት አምላክና የክብር ንጉሥ እርሱን ጎኑን በጦር ወጉት ቅዱሳት እጆቹን በመስቀል ላይ ዘረጋ ከኃጢአትም ነፃ ያወጣን ዘንድ በምስማር ተቸነከረ ፡ መስቀል ከበረ ፡ ዓለም ለድኅንነት ተጠራ ፡ እግዚአብሔር ተመሰገነ ሰው ነፃ ወጣ ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ኃይል ሰይጣን ታሰረ ።

## 11ኛ/ ስለትንሣኤው

ቅዱስ ያሬድ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ሲናገር መሠረተ ትምህርቱን በሐዲስ ኪዳንና በጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ትምህርት ላይ በመመሥረት እንዲህ ይላል ።
"ንሕነሰ ንሰብክ ክርስቶስሃ ዘተንሥአ እሙታን
መድኃኒተ ከነ ለእሕዛብ እመስቀሉ ወሪዶ ውስተሲኦል ሙቁሐነ ፈትሐ ሰበከ ሎሙ ግእዛነ ዘሐመ ወሞተ ወተቀበረ ፃዕረ ዘሞት ፈትሐ ወዘእምትን ተንሥአ ...

እኛ ግን ከሙታን የተነሣውን ክርስቶስን እንሰብ ካለን ክርስቶስ ለአሕዛብ መድኃኒት ሆነ ።

ከመስቀሉ ከወረደ በኋላ ወደ ሲኦል ወርዶ በሲኦል ውስጥ የታሰሩትን ፈታ ነፃነትንም ሰበከላቸው መከራ ተቀበለ ሞተ ተቀበረ የሞት ፃዕርን አጠፋ ከሙታንም ተለይቶ ተነሣ ......" (ጾመ ድጓ)

እንደዚሁም እጅግ ዝነኛ በሆነው መዝሙረ ትንሣኤ (መወድስ) ክርስቶስ በታላቅ ኃይልና ሥልጣን እንደተነሣ የሚከተለውን ተናግሯል ።
ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን
በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን
አሠሮ ለሰይጣን
አግአዞ ለአዳም ሰላም
እምይእዜሰ ይኩን ሰላም ።

ክርስቶስ በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ፤ ሰይጣንን አሰረው አዳምን ነፃ አወጣው ሰላም ከዛሬ ጀምሮ ይሁን ሰላም"

## 12ኛ ስለ ዕርገቱና ነቢረ የማን

ንሕነሰ ነአምን በአሐዱ እግዚአብሔር አብ ዘላዕለ ኩሉ ወበወልዱ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒነ ዘሞተ ለነ ቤዛነ ቤዛ ኩሉ ኮነ ፤ ወመጠወ ነፍሶ በእንቲአነ ። ዮምሰ ዐባይ ትፍሥሕትነ እስ መተንሥአ ወዐርገ ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ ፤ ነሢአ ፤ ሥጋ እንተ እምኀቤነ ተለዐለ እምኀበአቡሁ ተሰብሐ ።

እኛ ግን ከሁሉ በላይ በሆነው በአንዱ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን ስለ እኛ በሞተልን በአንድ ልጁ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ። እርሱ የሁሉ ቤዛ ሆነ ስለ እኛ ሕይወቱን ሰጠ ። ዛሬ ትልቅ ደስታችን ነው ክርስቶስ ተነሥቶአልና ወደ ሰማይም ዐርጎአልና በአባቱም ቀኝ ተቀምጦአልና ። ከእኛ ሥጋ ይዞ ዐረገ ከአባቱም ዘንድ ከበረ "ንበር በየማንየ" ተባለ (ድጓ)

## 13ኛ/ ስለ መንፈስ ቅዱስ

ቅዱስ ያሬድ ስለ መንፈስ ቅዱስ ፡ አርያምና ዝማሬ በተባሉ ድርሰቶች ውስጥ በሰፊው ተናግሮአል እርግጥ በሌሎች ድርሰቶችም ስለ መንፈስ ቅዱስ በሚገባ ጽፎአል ። የቤተ ክርስቲያን ፍጹምነትን በመንፈስ ቅዱስ መሆኑን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ይላል ፦

".. ለዛቲ ቤት ሣረራ አብ ቀዲሙ ፤ ሐነጸ ወልድ ወፈጸማ መንፈስ ቅዱስ ፤

ይህችን ቤት አስቀድሞ አብ መሠረታት ወልድ አነጸት መንፈስ ቅዱስም ፈጸማት" ይህንም በመሰለ ሥርዓት በሌላ ክፍል የሚከተለውን ያስተምረናል ፤

"ሃይማኖት እንተ እምቦበ አብ ተወጥነት ኀበ ወልድ ታበጽሕ ኀበ መንፈስ ቅዱስ ትትፌጸም፣ እአብ ዘንድ የተጀመረች ሃይማኖት ወደ ወልድ ታደርሳለች በመንፈስ ቅዱስ ዘንድ ትፈጸማለች (ድጓ)

## 14ኛ/ ስለ ቤተ ክርስቲያን

"ትስግድ ለከ መካን እንተ ፌርየት በዕፀ መስቀልከ
ውነዝንት እንተ ተፈሥሐት በቅድሳቲከ
ወሕሥምት እንተ ሠነየት በሞትከ
ወዓመት እንተ ግእዘት በጽፍዐትከ
ተጸፋዕከ በእንቲአሃ በውስተ ዐውድ
ይእቲ ተቤዘወት በመስቀልከ
ወተሰይጠት በደምከ
ወተዐትበት በስምከ
ትበልዕ ኅብስተከ
ወተአምን ብከ ከመ ሥጋከ ውእቱ ዘትበልዕ
ወተአምን ብከ ከመ ደምከ ውእቱ ዘትሰቲ ወይትፈለጥ
ጣዕመ በውስተ አፉሃ በእንተ ሃይማኖተ ልባ ፤

መስቀልህን ያፈራች ቦታ ቤተ ክርስቲያን ትሰግድልሀለች ኀዘንተኛ ነበረች ግን በቅድስናህ ደስተኛ ሆነች ጎስቋላ ነበረች ግን በሞትህ ተዋበች ለኃጢአት ተገዢ ነበረች ግን በጥፊ በመጾፋትን ነፃ ወጣች ስለ ርስዋ በዐደባባይ በጥፊ ተመታህ በመስቀልህና በደምህ ተዋጀች በስምህ ከበረች ኅብስትህን ትበላለች የምትበላውም ኅብስት ሥጋህ እንደሆነ ታምናለች የምትጠጣውም ወይን ደምህ እንደሆነ ታምናለች ። ስለ ልብዋ እምነትም ጣዕሙ በአፋዋ ይለወጣል ፤

## 15ኛ/ ስለ ምሥጢረ ጥምቀት

"በደሙ ቤዘዋ ወበማይ ዘውሕዘ
እምገበሁ አጥመቃ
በደሙ ቤተክርስቲያንን ዋጀት ከጎኑ በፈ
ሰሰው ውኃም አጠመቃት ......"



# የድሆች ጠበቃ

ይህ ስያሜ ለዮሐንስ አፈወርቅ መሰጠቱን በታሪክ አምድ እንረዳለን ዮሐንስ የትውልድ ሀገሩ አንጾኪያ ነው ፤ ይህችም ሀገር አሁን በቱርክ ግዛት ትገኛለች የተወለደበትም ዘመን በ354 ዓ.ም. ነው ወላጅ አባቱ ሴኩንዱስ ሲሆን እናቱ ደግሞ አትናስያ (አንቱሳ ትባላለች ወላጅ አባቱ ሙያው ውትድርና ሲሆን የወታደሮች አለቃ ነበር ። በወታደሮችም ዘንድ እጅግ በጣም ተወዳጅነት ነበረው ፤ ይሁንእንጂ ልጁን ዮሐንስን ለማሳደግ አልቻለም ዮሐንስ እንደተወለደ ወዲያውኑ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል እናቱ ግን 20 ዓመት እስኪሞላው ድረስ እያስተማረች በሚገባ አሳድጋዋለች ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ወሰዳ እንዲያስተምርላት አደራ የሰጠችው ሊባንዩ ለሚባል አስተማሪ ነው ። ይህም መምህር በዚያን ጊዜ ከነበሩት መምህራን መካከል ከፍተኛ ዝና የነበረውና እጅግ በጣም ተወዳጅነት ያለው እንደነበር ይነገራል ። መምህሩ የእናቱን የአትናስያን (የአንቱሳን) ደግነት እየተመለከተ በሚገባ አስተምሮታል ከዚያም ቀጥሎ አንድራጋቲው ከሚባል አስተማሪ የፍልስፍናንና የሕግ ትምህርትን አጠናቆ ተምሮ በሕግ ትምህርት ዶክትሬትን ተቀብሏል ።

ዮሐንስ አፈወርቅ የሕግ ዶክትሬቱን ከተቀበለ በኋላ የሰው ልጆች ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን የሚያባክኑት ሕግን ባለማወቃቸውና በሕግ ባለመጠቀማቸው ነው ፤ ስለዚህ ሕግን ተምሮና አውቆ ድሆችን በጥብቅና ሙያ ማገልገል ከሁሉ የበለጠ መንፈሳዊ ተግባር ነው በማለት በጥብቅና ሥራ ተሰማርቶ ድሆችን ለማገልገል ጀምሮ ነበር ነገር ግን የጥብቅና ሥራም ቢሆን እውነትን የማይከተልና አንዳንድ ጊዜም ሕግን ሳይከተል በአነጋገር ፈሊጥ ብቻ እየተመራ ድሆችን የሚበድል ሆኖ ስላገኘው ጥብቅናውን ትቶ በአንጾኪያ ወደሚገኙት ከፍተኛዎች ቦታዎች በመዘዋወርና አንዳንድ ነገሮችን በመቅሰም ለአራት ዓመታት ያህል ቆየ ከዚያም በኋላ ሁለት ዓመታት በዋሻ ውስጥ ዘናቶ በመጸለይ ወደፊት ስለሚሠራው ሥራ መሪ የሚሆን ትእዛዝ ከፈጣሪው ተቀብሏል ።

በ380 ዓ.ም. እንደገና ወደ ተወለደበት ቦታ ተመልሶ ማስተማሩን ቀጥሏል ዮሐንስ አፈወርቅ የዲቁናን መዓርግ በተቀበለ በ10 ዓመቱ በ381 ዓ.ም ስለምንኩስናና ስለመነኮሳት ስለ ሥልጣነ ካህነትና ስለካህናት መንፈሳዊ አገልግሎት ድርሰት መጻፍ ጀምሯል በዚህም ድርሰቱ ከዚህ በፊት ከሰባት ዓመት ጀምሮ የዲቁና መዓርግ ይሰጥ ስለነበር ። ልጆች በሰባት ዓመታቸው የዲቁና ሥልጣንን መቀበል እንደማይገባቸውና ቀሳውስትም ከመቅሰሳቸው አስቀድመው የቤተ ክርስቲያንን ምሥጢራት አውቀው ለማሳወቅ የሚበቁ እንዲሆኑ ፤ ካላወቁ ግን ሥልጣን ክህንነትን መቀበል እንደማይገባቸው በድርሰቱ አስፍሯል ።

ዮሐንስ አፈ ወርቅ በ386 ዓ.ም ፍላቪያን ከሚባል ኤጲስ ቆጶስ የቅስናን መዓርግ ከተቀበለ በኋላ ከመጀመሪያ ይዞታው አስበልጦ ስለአስተማረ ከአፉ በሚወጣው ኃይለ ቃል እጅግ በጣም የተወደደና ዝነኛ ለመሆን በቃ ከመልካም ዝናውም የተነሣ ብዙ ሰዎች ከሩቅ ሀገር እየመጡ ትምህርቱን ያዳምጡት ነበር ። እርሱም አዘውትሮ የሚያስተምረው በዚያን ጊዜ ዝነኛ በነበረችው ቆስጠንጢኖስ ባሳነፃት ቤተ ክርስቲያንና በአንጾክያ አካባቢ በሚገኙት አብያተ ክርስቲያን እየተዘዋወረ ነበር ።

በዕለተ እሑድ በበዓላትና በዓቢይ ጾም እንዲሁም ብዙ ሰዎች በሚገኙበት ቦታ እየተገኘ በማስተማሩ ሕዝቡ ሁሉ በትምህርቱ አመደሰታቸው የተነሣ "የሁሉ አፍ" እያሉ ይጠሩት እንደነበር ስለእርሱ የተጻፈው ታሪክ ያስረዳል።

ጥቂት ቆይቶም "ክረሶስቶም" የሚል ስም ተሰጥቶታል ። ይህም አፈ ወርቅ ማለት ነው ዮሐንስ አፈወርቅ ቅስናን በተቀበለ በ12 ዓመቱ በ398 ዓ.ም በአንጾኪያ ሆኖ መጻሕፍተ ብሉያትንና ሐዲሳትን በሚገባ አብራርቶ ተርጉሟል መጻሕፍትን መተርጐም ብቻ ሳይሆን እርሱ ስለሚሥጢረ ክህነት ስለዕለተ ሰንበትና ስለበዓላት አከባበር ስለሃይማኖት ስለ ፍቅር ስለሕግ ስለድሆች ስለእውነትና ስለመሳሰሉትም ሰፋ ያለ ድርሰትን ደርሷል በዚያ ጊዜ ሕግ ጠባቂዎች ሲደሰቱ ሕግ አፍራሾች የሆኑ ሰዎች በጠላትነት ተነሥተውበታል ።

በሰው ዘንድ እንዲጠላ ካደረጉትም ነገሮች አንዱ ስለአንዲት ድሃ ሴት ያደረገው ትክክለኛ ተቃውሞ ነው በዚያ ዘመን የነበረችው አውዶክስያ የተባለችው ንግሥት በሥልጣኗና በሀብቷ በመመካት የአንዲቱን ድሀ ሴት ርስት በግፍ ነጥቃ ስትወስድባት ዮሐንስ በመመልከቱ እግዚአብሔር እውነት ፈራጅ በመሆኑ በእርሱ አርአያና ምሳሌ የተፈጠሩ የሰው ልጆች ሁሉ በእኩልነት እንዲኖሩ ፈቃዱ ነው እንጂ አንች በሥልጣንና በሀብት ተመክተሽ ያለ ፈቃዷ የድሃይቱን ርስት ልትቀሚያት አይገባሽምና መልሺላት ብሎ መላልሶ ቢመክራት አልቀበልም ስላለችው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስን ሥጋና ደም እንዳትቀበል ወደቤተ ክርስቲያንም እንዳትገባ አወገዛት ።

አውዶክስያም ከእርሷ ጋር በጥቅም የተሳሠሩትን 26 ኤጲስ ቆጶሳት ሰብስባ በዮሐንስ አፈወርቅ ላይ ውሳኔ ስላስተላለፉ ወደ ደሴተ አጥራቅያ (ወደ ጥቁር ባሕር) አካባቢ ወደ ምትገኝ ደሴት ተሰዶ ከኖረ በኋላ እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር መስከረም 14 ቀን 407 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል በሚሞትም ጊዜ "ስላደረገልኝ መልካም ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይሁን" የሚለውን ቃል ተናግሯል ።። ቅዱስ ዮሐንስ አፈ. ወርቅ በርከት ያሉ ድርሰቶችን ለቅ



www.ethiopianorthodox.org

ድስት ቤተ ክርስቲያን አበርክቷል ያበረከታቸውም ድርሰቶች ከአሥራ ስምንት ሸልዩም እንደሚበልጡ ስለእርሱ ከተጻፈው ታሪክ ለመረዳት ይቻላል ድርሰቶቹም በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ተመድበው ይነገራሉ ፤ አንደኛውና የመጀመሪያው ብሉያትንና ሐዲሳትን አጠቃሎ የያዘ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ስለ ሥላሴ አንድነትና ሦስትነት ስለ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ስለሥርዓተ ሃይማኖትና ስለሞራላዊ ግዴታ ሰፋ ባለ ሁኔታ የሚያስረዳ ነው ።

ባሮችና ጌቶች ወንዶችና ሴቶች ትንንሾችና ትልልቆች በቤተ ክርስቲያን አመለካከት ሁሉም እኩል ናቸው ሲል ዮሐንስ አፈወርቅ በድርሰቱ መላልሶ ጽፏል በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያን ከፍተኛ ዝና አላቸው ተብለው የሚጠቀሱት ሦስት ታላላቅ አባቶች ሁለቱ ቅዱስ ባስልዮስና ቅ. ጎርጎርዮስ ዘእንዜናዙ ሲሆኑ ሦስተኛው እርሱ ነው ። ስማቸው የተጠቀሰው አባቶች ለቤተ ክርስቲያን ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ስላበረከቱ እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ኅዳር 13 ቀንና ጥር 30 ቀን በአንድነት ሦስቱም ይከበራሉ ።

ደጋግ ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን ያበረከቱት መልካም ሥራ ሁሉ በትውልድ ሀገራቸው ብቻ አይወሰንም መልካም ሥራቸው ትሩፋታቸው ዓለም አቀፍ በመሆኑ ለመላው ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ተደርሷል ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በእንዶኪያ ሆኖ ያስተማረው ትምህርት የደረሰው ድርሰት የፈጸመው ምግባር ትሩፋት ሁሉ በጠቅላላው በዚያው ሳይወሰን በእኛም ቤተ ክርስቲያን ከፍ ያለ ቦታ ተሰጥቶታል ዮሐንስ ከባለ ጸጐች ይልቅ ለድሆች የሚያዝንና የሚራራ ስለድሆች እንደጠበቃ ሆኖ የሚከራከር ስለነበር ከሰዎች ዘንድ የድሆች ጠበቃ የሚል ስያሜ እንዳገኘ ተጽፎአል ፤ ዮሐንስ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አባት የእርሱን አሠረ ፍኖት ተከትሎ ችግረኞችን በመርዳት የድሆች ጠበቃ የሚለውን ስያሜ ለመቀዳጀት መጣምር ይኖርበታል ።

ቄ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ

# ልደታ ለቅድስት ..

ከገጽ ፱ የዞረ

"እግዚአብሔር ለየዋሐን ቅርብ ነው ጆሮዎቹም ወደ ልመናቸው ነው እንደተባለ" በንጹሕ ልብ ሆነው የለመኑትን የኢያቄምና የሐናን ስእለት ሰማ፡ ስለዚህም እንደ አምስቱ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ትውፊታዊ ትምህርት ቅድስት ሐና ነሐሴ ሰባት ቀን ፀንሳ ግንቦት አንድ ቀን ቅድስት ድንግል ማርያምን ወለደች ።

የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መወለድ ለጊዜው ለኢያቄምና ሐና ታላቅ ደስታ ሆኖአል በፍጻሜ ግን ለዓለም ሁሉ ፍጹምና እውነተኛ ደስታ ነው የዓለም ደስታ ክርስቶስ ከእርስዋ ተወልዶአልና ቅድስት ድንግል ማርያም ለጊዜው ለኢያቄምና ሐና ጸጋና በረከት ሆና ከእግዚአብሔር ተሰጥታለች በኋላ ግን ለዓለም ሁሉ ጸጋና በረከት ሆናለች ። በእርሱ አዳኝነት በእርስዋ አማላጅነት ለሚያምኑ ሁሉ ጸጋና በረከትን የሚያድል ክርስቶስ ከእርስዋ ተወልዶአልና ። የቅድስት ድንግል ማርያም ልደት ለድኅነት ዓለም ምክንያት ነው ክርስቶስ ከርስዋ ተወልዶ ዓለምን አድኖአልና ። ይህም አስቀድሞ በተስፋ ተነግሮአል ። የመጀመሪያው ሰው በኀጢአት በወደቀ ጊዜ እግዚአብሔር የሚከተለውንም የተስፋ ቃል ሰጠው ቃሉም"...ከልጅ ልጅህ እወለዳለሁ በመስቀሌና በሞቱም አድንሃለሁ" (ዘፍ. 3፡15 ቀሌም) የሚል ነው። ከዚህ ላይ የልጅ ልጅ የተባለችው ድንግል ማርያም መሆንዋ ግልጥ ነው። በዚህም መሠረት በድንግል ማርያም የአዳም ተስፋ ተፈጽሞአል ። የአዳም ልጅ ብቻ ሳይሆን የአዳም ልጆች ሁሉ ተስፋ በእርስዋ ተፈጽሞአል ። ባጠቃላይ የድንግል ማርያም መወለድ የዓለም በረከት ጸጋና ደስታ የተስፋም ፍጻሜ ነው ክርስቶስ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ዓለምን አድኖአልና ።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

# የጥንታዊው ደብረ ሊባኖስ

ከገጽ ፲፭ የዞረ

ለሚመለከተው ክፍል ውሳኔ ያስተላልፋሉ ። ከላይ ምርፋቆች የሚጸልዩበትንና የሚሰበሰቡትን ቦታ ጠቅሰናል በተለይ መስቀል ቤት ምን እንደሆነ ለማብራራት እንሞክራለን መስቀል ቤት የሚባለው 1ኛ ጻድቁ ተ ሃይማኖት የተከሏት ታቦተ ማርያም 2ኛ ከሰማይ ወረደ የሚባል የእንጨት መስቀል ቅርጹ በሰው እጅ የተሠራ የማይመስል 3ኛ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የእጅ መስቀልና የተለያዩ ንዋያተ ቅድሳት ይገኙበታል ቤቱም በመስቀል ቅርጽ የተሠራ ነው ። ከሰማይ ወረደ የሚባለው መስቀል ሁል ጊዜ እንደማይወጣ ለማስረዳት ያህል በሦስት በዓላት መንኰሳት የመስቀሉን ክብር ለመግለፅ በዋዜማው ጀምሮ ምን ዓይነት ሥርዓት እንደሚያካሒዱ ገልጸዋል ።

ይህም መስቀል በወጣ ጊዜ ለምጻም ያነፃል ዕውር ያበራል ድውይ ይፈውሳል በጠቅላላ ሕሙማንን ያድናል ።

የጻድቁ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የእጅ መስቀልም "አፍሮ አይገባ" የሚል ስም ተሰጥቶታል ምክንያቱም ከወጣ ፈውስ ሳያደርግ እንደማይመለስ ከአባቶችና ከበሽታቸው ከዳኑ ሰዎች ለመረዳት ችለናልና ነው ።

በዚህ በታላቅ ገዳም ጐላ ብለው የሚታዩትን ቅርሶችና መስቀሎች ጠቀስን እንጂ ያሉትን ንዋያተ ቅድሳት በዚህ ጽሑፍ መዝግቦ ለማቅረብ ብዙ ቀናት ስለሚጠይቅ በዝርዝር ለማቅረብ አልቻልንም ።

በሁለተኛው ገጽ በጠቀስነው መሠረት የጥንቱንና የአሁኑን ገዳማዊ ኑሮ በማነፃፀር እናቀርባለን ግን ልዩነት አለው ማለት ሳይሆን ጠይቀን ያገኘነውን መልስ ለመግለጽ ያህል ነው ።

አባቶችን ልዩነቱ ምንድር ነው? ብለን ስንጠይቃቸው የሰጡን መልስ በገዳማዊ ኑሮ በኩል ምንም ልዩነት የለም ዛሬም ከሸዋ ሀገረ ስብከት መንግሥት ለካህናት ከሚሰጠው በዓመት ብር 12000 (አሥራ ሁለት ሺህ ብር) ከቤት አበል በወር 600 (ስድስት መቶ ብር) እናገኛለን ስለ አስተዳደሩም የአስተዳደሩ መዝገብ እንደሚያስረዳው ልዩነት እንደሌለው ያመለክታል ።

## የድርጐኞችና የመነኰሳት ብዛት

በዚህ ገዳም ውስጥ በአጠቃላይ ቀለብተኞች 500(አምስት መቶ ናቸው)በነዚህ ውስጥ መነኰሳቱ 245 ሲሆኑ ጥቁር ራስ ወይም አርድእቱ 255 መሆናቸውን ሊቀ ዲያቆን አባ መሐሪ ገ/ ማርያምንና ጸሐፊውን አነጋግረን መዝገቡን ስላሳዩን በመዝገብ የሠፈረው ቁጥር ከላይ የተጠቀሰው መሆኑን ተመልክተናል ። ሆኖም የማኅበሩን የምግብ አሰጣጥና አመጋገብ ከመግለፃችን በፊት አሁን ያሉትን መምህራንና የጸሎቱን ሥነ ሥርዓት ከገለጽን በኋላ ስለ አራቱ ተግባር ቤት ሁኔታ ዝርዝር እናቀርባለን ።

አለቃ አላቸው ግን የሚሾማቸው መጋቢ ነው ። ታዲያ የገዳም ኑሮ ስለሆነ ሹመት እንጂ ከሌሎች የተለየ ደመወዝ የለም የሚጋግረውም ወጥ የሚሠራውም የሚያነፍረውም የውሃ ክፍሉም የሚያገኙት እንደሌሎች መቁነን ብቻ ነው።

## በዚህ ገዳም ውስጥ የተለያዩ መምህራን አሉ እነሱም

| | |
|---|---|
| 1 - አለቃ ጥበቡ አስናቀ | የብሉይ መምህር |
| 2 - " ብርሃኑ | የሐዲስ " |
| 3 - " መኰንን | የድጓ " |
| 4 - " በትረ ገ/ መድኅን | የአቋቋም " |
| 5 - " መርዓዊ ሣህለ ሚካኤል | " " |
| 6 - " ምሕረት ደስአለኝ | የቅኔ " |
| 7 - " ዓምደ ሀ/ ማርያም | " " |
| 8 - አባ ወ/ ገብርኤል ያለው | የዝማሬ መዋሥዕት |
| 9 - መሪጌታ ነቅዓ ጥበብ ደምሴ | የቅዳሴ" |
| 10 - አባ ኢያሱ እሰፋ | የንባብ " |
| 11 - መሪጌታ ተከሥተ ካሣ | " " |
| 12 - አባ ፃ/ ማርያም ሀ/ ሚካኤል | " " ናቸው |

በእነዚህም መምህራን የሚማሩ ተማሪዎች ከ150 (ከአንድ መቶ አምሳ) በላይ እንደሚሆኑ ተነግሮናል ። ከዚህ ላይ ለመግለጽ የምንፈልገው ተማሪዎቹ መቁነን አለማግኘታቸውን ነው ። ነገር ግን ተማሪዎቹ በታመሙ ጊዜ በሊቀ አበው አማካይነት እስከሚድኑ ድረስ ምግብ ይሰጣቸዋል ።

## አሁን የሚካሄደው የጸሎትና የሰዓታት ሥነ ሥርዓት

የጸሎት ሥነ መርዓት በዘወትር ቀን የሚካሔደው ከጠዋቱ በ12 ሰዓት ከቀኑ በ10 ሰዓት ነው ይኸውም የማኅበር ጸሎት እንጂ በተለያዩ ጊዜያት እንደሚጸለይ ከላይ በጠቀስነው ያንብ መመልከት ይቻላል ። የሰዓታቱም ሥነ ሥርዓት እሑድ ከሌሊቱ በ3 ሰዓት ይጀመራል ። ቅዳሜ በ4 ሰዓት ይጀመራል በሌላው ቀን በዘወትር በ6 ሰዓት ይጀመራል ማኅሌቱን ግን እንደ ክብረ በዓሉ እየታየ እንደሚከናወን ተመልክተናል ።

## አራቱ ተግባር ቤት

ሀ - የእንጀራ ቤት

ለ - የወጥ ቤት

ሐ - የንፍሮ ቤት

መ - የውሃ ክፍል ናቸው ለእነዚህ ሁሉ የተለየ ሌሎችም ሠራተኞች አናኰ - እንጨት (ሰባሪ) እንጨት የሚጭን በበቅሎና በአህያ እህልና ሌላም የሚያመጡ እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ ኑሮአቸው እንደመነኮሳቱ ነው ።

ከላይ እንደጠቀስነው 500 ሰዎች መቁነን ያገኛሉ ብለናል እነዚህ ሁሉ ልክ ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት ወደተግባር ቤት እየሔዱ የአንድ እንጀራ አንድ አራተኛ ወይም አንድ እንጀራ ከአራት ተቆርሶ ያችንና አንድ እፍኝ ንፍሮ ብቻ ተቀብሎ አምጥቶ መመገብ ነው ። ቁርስ የለም እራት የለም ሁሉም በዚህ ዓይነት የተወሰነ ነው የሚገርመው ደግሞ ሊጥ የሚቦካበት ገንዳ አይከደንም የተከደነ እንደሁ ትል ይሆናል ይላሉ ግን ገንዳው ጸሎተ ዕጣን እየተደገመ እንደ ሚታጠን ተመልክተናል የንፍሮውም ውሃ አይገኝም እንጂ የሆድ ሕመም ያለበት ሰው ሲጠጣው ከበሽታው እንደሚድን ከዳኑት ሰዎች መካከል ጠይቀን ተረድተናል ።

## ፀበሎች

በደብረ ሊባኖስ ገዳም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ብዙ ፀበሎች እንዳሉ እየተዘዋወርን ተመልክተናል ። ፀበሎችም በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘመን እንደፈለቁ ይነገራሉ ።

ፀበሎችም ሀ - ዮርዳኖስ ለ - ገፋዓን ሐ - ኤላም መ - ባሕታዊ ሠ - እንቁርቁሪት ተብለው ይጠራሉ ከእነዚህም ፀበሎች መካከል በጣም በአሁኑ ጊዜ ሰዎች እየተጠመቁ ከበሽታቸው የሚድኑባቸው ዮርዳኖስና ኤላም ከተባለው ቦታ አጠገብ ያሉት ናቸው ሕመምተኞች በፀበሎቹ ብቻ ሳይሆን ከቤተ ክርስቲያኑ ማለት ከምድር ቤቱ ገድለ ተክለ ሃይማኖት ሁልጊዜ ጧት ጧት ስለሚነበብ ገና ሲጀመር የሚጮኹት በሽተኞች ብዙዎች ናቸው ጮኸውም ብቻ ሳይቀሩ ተነቦ በመስቀል በታሹ ጊዜ ከሕመማቸው እየዳኑ እልልታቸውን እያሰሙ የሚሔዱ እንዳሉ የዓይን ምስክር በመሆን ተመልክተናል ።

የደብረ ሊባኖስን ገዳም ታሪክና የአካባቢውን ሁኔታ በዚህ አጭር ጽሑፍ ለመወሰን አይቻልም ቢሆንም የተለያዩ የቅዱሳን አጽም ያለበትና የበቁ መናንያን ስለሚኖሩበት አኩሪ ቦታ ነው ለማለት ይቻላል ። በተለይ አዘቅት ከተባለው ሥፍራ ሔዶ ለተመለከተው ሰው የብዙ ቅዱሳን አጽም ይታያል እንዲያውም የብዙ ዓመታት ግምት ያለው አንድ ሬሳ ለምልክት ያህል እንዳለ ሁለት እግሮቹ ብቻ ከጉልበቱ በታች አጥንት ሲሆን ሌላው ግን አንድ እጁን ከጭኑ ላይ አንድ እጁን ከአፉ ላይ ጣል እንዳደረገው ከነሥጋው ደርቆ ይታያል ግን መግቢያ ስለሌለው ቀርቦ ለማየት አስቸጋሪ ነው ።

ታዲያ እንደዚህ ያለውን ቦታ መንከባከቡ የአካባቢው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የመላ ኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ጭምር ነው ። በአሁኑ ጊዜም በገዳሙ አንዳንድ ችግር እንዳሉ ተመልክተናል የውሃ ወፍጮዎች ቆመዋል ። ለቤተ ክርስቲያኑና ለሌላ አገልግሎት የሚውለው ኤሌክትሪክ ተቋርጧል ይህ ሊሆን የቻለው እዚህ ይውል የነበረውን ውሃ ሌሎች ግለሰቦች እንጠቀምበታለን በማለት ስለተከፋፈሉት መሆኑን ከገዳሙ ማኅበር ለመረዳት ችለናል። ቢሆንም እአንድ ሺህ በላይ ለሚኖሩ ሰዎችና ለቤተ ክርስቲያን ግልጋሎት የሚሰጠው ጥቅም መቋረጡ አሳሳቢ በመሆኑ የሚመለከተው ክፍል ቢያስብበት መፍትሔ እንደሚያገኝለት አይጠረጠርም በማለት እያሳሰብን ስለሴት ደቤር ታሪክና ተግባር በአጭሩ ለአንባቢያን ለማቅረብ እንፈልጋለን ።

## ሴት ደቤር

ይህ ገዳም መታሰቢያነቱ የእቴጌ ጣይቱ ብጡል እንደሆነ የታሪክ መዛግብት ያረጋግጣሉ አባቶችንም ጠይቀን ትክክለኛ መሆኑን ተረድተናል ይህ የሴት ደብር በግምት ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን 2 ኪሎ ሜትር ርቆ ይገኛል ።

በገዳሙ ጡረተኞች መነኮሳይያትና በድንግልና ተወስነው የሚኖሩ መነኩሳይያት ናቸው ።

በገዳሙ ውስጠ የደብረ ገነት ማርያምና ኪዳነ ምሕረት አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ ።

ወደ ገጽ ፳፱ የዞረ





www.ethiopianorthodox.org

# ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ዐርጋለሁ

ዮሐ 20 ፥ 17

ከሰማየ ሰማያት የወረደው
የሰውን ደካማ ሥጋ የተዋሐደው ፤
ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ፤
በዓለም ዙሪያ ተመላልሶ ወንጌልን የሰበከው ፤
ሀሰትን አፈራርሶና አጥፍቶ እውነትን የመሠረተው ፤
ስለእኛ በደል ሲል በመስቀል ላይ ደሙን ከሶ ፤
የሚቃወመንን የዕዳ ደብዳቤ ደምስሶ
የኀጢአትን ማሰሪያ ቆራርጦና በጣጥሶ ፤
በእኛና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን የጥል ምሶሶ
ከመሠረቱ ላይ ነቅሎ ግድግዳውንም አፈራርሶ ፤
ከአባቱ ጋር አስታርቆን
የተዘጋውን የገነትን በር ከፍቶልን
ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ዐርጋለሁ
ለእናንተም ሥፍራን አዘጋጃለሁ ፤

ዮሐንስ 14 ፥ 1-3

በማለት ሐዋርያቱን ተሰናብቶአቸው
በመላእክት እየታጀበ የእጁ ሥራ በሆነው ፤
በብሩህ ደመና ተከቦ ተሠወራቸው ።

-በእርግጥ በአለፈው ውድቀታችን መጨነቅ እንዳይኖርብን
-እርጌውንና የዛገውን በአዲስ ሕይወት ቀይሮልን
-ከሁሉ በላይ አድርጐንና አክብሮን
- በመስቀል ላይ ራሱን አሳልፎ የሰጠው መድኃኒታችን ሉቃስ 24፥1-7
- ድንጋዩን ፈነቃቅሎ አፈላልሶ መቃብሩን ፤
- እንደ ተነሣ ሁሉ በሦስተኛው ዕለት ድል ነስቶ ሞትን ፤
- በስልጣኑና በፈቃዱ የሞተው ሊሆን የዓለም መድኃኒት ፤
- ዳግመኛ እንደሚመጣ ተናግሮ ለአዳም ዘር ሁሉ ለራሱ ፍጥረት ፤
- ተጽፎ እንደምናየውና እንደምናነበው በቅዱሳት መጻሕፍት ፤
- ስለበደላችን መከራ የተቀበለው
- እንደሚታረድ ጠቦት በሚወጉት ፊት የታገሠው
- ተጠማሁ ባለ ጊዜ መራራ ሐሞት የቀመሰው
- ሞሶና መቃብርን አጥፍቶ የተነሣው ።
-አርባ ቀን ሙሉ በምድር ላይ ተመላልሶ ፤ አረጋግጦ መነሣቱን ፤
- አሳውቆ አስረድቶ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን ፤
- እንዲሁም አሳፍሮአቸው ጸሐፍት ፈሪሳውያንን ፤
- አስተባብሎ ከንቱ የፈጠራና የቅናት ወሬአቸውን ፤
- ዳግመኛ እንደሚመጣ አስረድቶአቸው ሀቁን ፤
- በብሩህ ደመና ተከቦ ተጐናጽፎ ብርሃን መለኮቱን ፤
- ወደ ሰማይ ዐረገ እየባረከ ደቀ መዛሙርቱን

ተማሪ ሊባኖስ ገዳሙ

## መንፈስ ቅዱስ …

ከገጽ ፫ የዞረ

ቶስ በዚህ ዓለም እየተመላለሰ በሚያስተምርበት ወቅት የቅርብ ተከታዮቹ እንደመሆናቸው መጠን ሕሙማንን ሲፈውስ ልዩ ልዩ ተአምራት ሲያደርግ አይተዋል ። ሁለት አሣና አምስት እንጀራ አበርክቶ አምስት ሺህ ሰው ሲያጠግብ እነርሱም የምግቡና የረድኤቱ ተካፋዮች ነበሩ ። ምንም እንኳ ይህንን ሁሉ ነገር ቢመለከቱ ልባቸው በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት ገና ስላልተቀጣጠለ የዚህን ዓለም ክብር የዚህን ዓለም ደስታ ለማግኘትና ከሰው በላይ ሆኖ ለመታየት የሥልጣን ሽሚያ ያደርጉ እንደነበር ግልጽ ነው ።

የያዕቆብና የዮሐንስ እናት ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ከልጆቿ ጋር ሄዳ አንዱ በቀኝህ አንዱ በግራህ እንዲቀመጡ ፈቃድህ ይሁን ብላ በእማላጅነት እንድትጠይቅላቸው እንዳደረጉ መጽሐፍ ይነግረናል የማቴ.ወ.ምዕ. 20 ቁ.20 ።

በሌላ በኩል ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ እራት ባደረገበት ምሽት ደቀመዛሙርቱ በገበታው ዙሪያ ተቀምጠው የማእዱን የፅዋው ተካፋይ ሆነው ሲጋበዙ አምሽተዋል ። በዚህም ምሽት የሚሞት መሆኑን በነገራቸው ጊዜ ጴጥሮስ ብቻ ሣይሆን ሁሉም አብረውት እንደሚሞቱ ቃል ገብተው ነበር ።ይሁን እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ስለ አልታደሱና በእምነት ስለአልጐለመሱ በተያዘ ጊዜ ሁሉም ጥለውት ሸሹ ። ከተነሣም በኋላ ደቀመዛሙርቱ አይሁድን ስለፈሩ ቤት ዘግተው የሚመጣላቸውን ተስፋ ከመጠባበቅ ያቀሩ ስለሞቱም ስለ ትንሣኤውም በአደባባይ አልመሁነሩም። ነገር ግን "በዓለ ሃምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ ዐውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምጽ መጣ ተቀምጠው የነበሩትንም ቤት ሁሉ ሞላው እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳናት ታዩአቸው በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው በሁሉም መንፈስ ቅዱስም ላባቸው መንፈስ ይናገሩ ዘንድ እንደ ተሰጣቸው በሌላ ልሳናት ይናገሩ ጀመሩ "የሐ.ሥራ ምዕ. 2 ከቁ 1-4 ፥ መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት ሆኖ በላያቸው ካረፈና በልባቸውም ውስጥ ገብቶ ከተቀጣጠለ በኋላ እርጌ የነበረው ሕይወታቸው ታደሰ መንፈስ ቅዱስም አዲስ ልብ አዲስ ሕይወትም ፈጠረላቸው ወንጌልን ለማስተማር ስለ ስሙ ስለ ጌትነቱም ለመመስከር መንፈስ ቅዱስ ኃይልና ብርታትን ሰጣቸው ። መንፈስ ቅዱስ እፍና ጥበብ እየሆነ በድፍረት ስለሚናገሩ ምን እንደሚናገሩ አልተጨነቁም በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት ህይወታቸው ስለ ተቀጣጠለ ረሃብ ፤ ስደት ፤ ሞት ፤ ከክርስቶስ ፍቅር ሊለያቸው አልቻለም መራራ የሆነውን ዓለም በትምህርታቸው አጣፍጠውታል ። ጨለማ የሆነውንም ዓለም በሥራቸው አብርተውታል ።

እንግዲህ ወደ ራሳችን ሕይወት መለስ እንበልና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዳችን እንደ ሚሰጥ እንዲህ ይላል ። ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር ይሰጠዋል ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ ለአንዱም ተአምራትን ማድረግ ለአንዱም ትንቢትን መናገር ለአንዱም መናፍስትን መለየት ለአንዱም በልዩ አይነት ልሳን መናገር ለአንዱም በልሳናች የተነገረውን መተርጐም ይሰጠዋል ። ይህ ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል ይላል። ስለዚህ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለእያንዳንዳችን በመንፈስ ቅዱስ ይሰጠናል ። ግን በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት አእምሮአችን ካልታነጸ አእምሮአችን ስለሚዝግ እኛ ቀዝቅዘን ሌላውን እናቀዘቅዛለን እኛው በድን ሆነን ሌላውንም በድን እንዲሆን እናደርጋለን ። ይህ እንዳይሆን በራሳችን ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ብርሃን ይብራ ይቀጣጠል። ሥራችሁ በሰው ፊት ይብራ ተብሏልና አለቃ ነብየ ልዑል ዮሐንስ

## የጤና ዓምድ

ከወ/ት ንብረት አበበ

በመልካም ጤና ውጤት የረጅም ዕድሜ ባለቤቶች ለመሆን ብንፈልግ በምግባችን በኩል እግዚአብሔር ለሰው ልጆች እንዲሆን የፈቀደው ምግብ ምን እንደሆነ ከዘፍጥረት 1 ፥ 29 ምን እንደሚል እንመልከት እነሆ መብል ይሆናችሁ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ ዝሩ በእርሱ ያለውን ለምለም ሁሉ የዛፍንም ፍሬ የሚያፈራውንና ዘር ያለውንም ዛፍ ሁሉ ሰጠኋችሁ የሚል ቃል እናገባለን ይኸውም የሚያስረዳው ለሰው ልጆች ምግብነት ተስማሚና ጤና ለሰው የሚሆነው ከእርሻ የሚገኝ እህልና ጥራጥሬ እንዲሁም አትክልት ቅጠላቅጠልና ፍራፍሬ መሆኑን እንጂ ከእንስሳት የሚገኝምግብ-ሥጋ)እንዳልሆነ እንረዳለን በእግዚአብሔር ጥንታዊ ዕቅድ ውስጥ ሥጋ ለምግብነት አልተመደበም ነበር ከጥፋት ውሃ በሁዋላ ግን እፅዋት ሁሉ ስለተነቃቀሉና በእሥራኤልም የሥጋ መጐምጀት ምክንያት የሥጋ ምግብነት ተፈቀደ ።

ቢፈቀድም እንኳ ያለው ጠቃሚነትና ጤና በመጀመሪያ እንድንመገባቸው ከተፈቀዱልን ምግቦች አይበልጥም ነበርና እስራኤላውያን እንዲበሉ የተመኙትን ሥጋ ካገኙ በኋላ የሰውነት መከሳት አግኝቶአቸዋል ከዚህ የምንረዳው የሥጋ ምግብነት ከሌሎች ምግቦች አለመብለጡን ነው ሥጋ ለምግብነት ቢፈቀድም ጤነኛ ሥጋ ለመብላት ዘወትር ስለማያጋጥም ለአንዳንድ በሽ

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል

## ቅዱስ ያሬድና …

ከገጽ ፲፰ የዞረ

(ጸመ ድጓ) በማለት ጌታችን በጦር በተወጋ ጊዜ ከጎኑ የፈሰሰውን ውኃ በማየ ጥምቀት ተርጉሞ አስተምሮአል።

### 16ኛ/ ስለ ክርስቶስ ምጽአት ስለ ትንሣኤ ሙታንና ፍርድ

"አመ ዕለተ ፍዳ ወአመ ዕለተ ደይን
አመ ዕለተ እግዚአብሔር
ምንተ ንብላ ለነፍስ አመ ኢታድኅን
እም ወለታ
ወምድርኒ አመ ታገብእ ማኅፀንታ
ምንተ ንብላ ለነፍስ ።
አመ ይለብስ አብ ልብሶ፤ ፍዳ ወያሞጥ
ሕ ምጣሕተ በቀል
አመ ይወቅስነ በግርምት ዐውድ አሚሃ
ይትከሠት ወይሰጣሕ ምግባራቲነ
ወይትነበብ ኩሉ ዘገብርነ ..... እምጌሶ ለሰብእ ሰበ ይምሕር ነዳየ ወይገብር ሠናየ ።

በእግዚአብሔር የፍርድ ቀን ነፍስን ምን እንላታለን ። እናት ልጅዋን በማታድንበት ምድርም አደራዋን በምታስረክብበት አብ የፍርድ ልብስ በሚለብስበት በአስፈሪ ዐደባባይ በሚወቅስን ጊዜ ነፍስን ምን እንላታለን ። ያንጊዜ ሥራችን ሁሉ ይገለጣል ። ያደረግነውም ሁሉ ይነበባል ሰው ለድኃ ቢራራ መልካም ሥራም ቢሠራ በተሻለው ነበር"

ቅዱስ ያሬድ ይህንና እጅግ ብዙ የሆነውን ትምህርተ መለኮት (የቴዎሎጊያ ትምህርት) በሚገለጥበት ጊዜ የትምህርቱ ጥራት እንከን ሊወጣለት አይችልም የቅዱስ ያሬድ ድርሰት በዜማ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በትምህርተ መለኮትም የተመላ መሆኑን እነሆ ባጭሩ ለማስረዳት ሞክረናል። የያሬድ ትምህርት ከቀደሙትና በኋላ ከተነሡት የትምህርተ ሊቃውንት ትምህርተ መለኮት ጋር እኩልነት አለው ። ስለዚህ ለመዝሙር ብቻ ሳይሆን ለትምህርተ መለኮትም ልንጠቀምበት እንችላለን ።





www.ethiopianorthodox.org

## የጥንታዊው ደብረ ሊባኖስ...

ከገጽ ፳፩ የዞረ

ገዳሙ ቤተ ስሌሖምና ሴት ገዳም ጡረታ ቤት በሚል ስያሜ ይጠራል ።

ገዳሙ በ1901 ዓ.ም. ተመሠረተ ይህም ገዳም በሚመሠረትበት ጊዜ ሁለት ዓላማዎችን የያዘ እንደሚሆን መምሪያ ስለአለ አሁንም በዚያው መሠረት ይመራል ።


ሀ - የደከሙትን እናቶች ለመጦር ለ ይህን ዓለም ንቀው በገዳም ለመኖር የሚፈልጉትን ደናግሎች መቀበል ነው ። ግን ሊቀበል የሚችለው የተወሰነ ስለሆነ በምትክ መግባት እንጂ እንደተፈለገው ሊገባ አይቻልም ።

ዳማዊ ኑሮ ከደካሞችና ከበሽተኞች በቀር መቀመጥ አይፈቅድምና ነው ።

በአጠቃላይ የገዳም ኑሮ ሁሉንም በአንድነት በማኅበራዊ ኑሮ የሚመለከት ስለሆነ ገዳማዊ ኑሮ ለሌሎች መልካም አርአያ እንደሚሆን ግልጽ ነው ።

ግን ወደገዳማዊ ኑሮ ለመግባትና ለመመንኩስ ብዙ አመክሮ ያስፈልጋል ። በዚያው ለመኖር ከተፈለገ እስከ ሰባት ዓመት ገዳሙን ማገልገል ወዲያው መንኩሶ ለመመለስ ከሆነ እንደ ዕድሜው ልክ እየታየና ብቃቱ ተገምቶ ሊመነኩስ ይቻላል ። ይህ የገዳሙ ደንብ ነው ።

በመጨረሻ ለአንባቢያን ለመግለጽ የምንፈልገው የጻድቁን የአቡነ ተክለ ሃይማኖት አጠቃላይ ታሪክ ማቅረባችን ሳይሆን ከላይ እንደ ተገለጸው የሐዋርያነትና የመነኩስና ሕይወታቸውን ለማስተዋወቅና የገዳሙን ሕይወት



የደብረ ሊባኖስ ቤተ ክርስቲያን

ለመግለጽ ነው ።

በገዳማዊ ኑሮ በኩል ግን ከደብረ ሊባኖስ ገዳም ልዩነት የለውም ልዩነቱ በድኩማን ድርጅት ውስጥ ስለሚተዳደር እንክብካቤና ይዞታው ለየት ያለ ነው ። አመክሮው ልክ እንደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ነው የማኅበር ጸሎት ይከሐዳል ተአምረ ማርያም ይነበባል ። ሌላም የገዳማዊው ኑሮ በትክክል ይሠራል ።

ገዳም እንደመሆኑ ምግብ የሚሰጠው አንድ ጊዜ ብቻ ነው ። በዚህ ገዳም 208 ቀለብተኞች ወይም ድርጉኞች ይገኛሉ ማንኛውንም ሥራ የሚሠሩ ደግሞ የመንግሥት ሠራተኞች 50 ናቸው የገዳሙ አስተዳደር የሚመራውም መነኩሳት ነው ታዲያ በዚያ የሚኖሩት መነኩሳት በትርፍ ጊዜያቸው በአስተዳደሩ የሚሰጣቸውን ሥራ እመሥራት ወደ ኋላ አይሉም ምክንያቱም በገ

የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ታሪክ ግን ብዙ ጸሐፊዎች ምን ዓይነት ሚና እንደሚጫወቱ ጽፈውት ይገኛል ። ይሁን እንጂ ከተወለዱበት ዘመን አንስቶ እስከ አሁን ድረስ ሕያው ታሪካቸው በቤተ ክርስቲያንና በገዳማዊ ኑሮ ላይ ትኩረት ያለው ስለሆነ ይህንን ስንጽፍ ሌላውን ታሪክ ግን ለሌላው ትተነዋል

ገዳማዊ ኑሮ ለቤተ ክርስቲያናችን አከራ ነው ። ገዳም ለማኅበራዊ ኑሮ መሠረት ነው ፤ በገዳም የሚኖሩ ሰዎች እኩልነታቸው በሥራ የተተረጉመ ነው ። በገዳም የግል ጥቅም የሚፈልግ አይኖርም ። ጉልበት ሁሉ ለገዳሙ ይገበራል እካል በእግዚአብሔር ቸርነት ኢትዮጵያ ትቅደም ።

ታሪክ አቅራቢው ነቅዓ ጥበብ ወንድም ።

## ምን እንርዳዎ ...

ከገጽ ፲ የዞረ

በሚመጣው ፈተና መበርገግ አያስፈልግም ።

ስለዚህ እርስዎ በጥያቄዎ ላይ እንደገለጹት በሁለት መንገድ መዋለል ማለት በሥጋና በነፍስ ፈቃድ መካከል ነኝ እንዳሉት እርጎጥ ያሉት በዓለም እንጂ ከዓለም ውጭ አይደሉም ግን ዓለምን ያሸንፏት እንጂ አያሸንፍዎ ። እኔ ዓለምን እንዳሸነፍኩት እናንተም አሸንፋት ተብሎ ተጽፎአልና ። ዮሐ.16 ፥33

ደግሞ ወደገዳም መሄድ እንደሚፈልጉ በጥያቄዎ ላይ ጠቁመዋል ። ገዳም ማለት ካወቁበት እርስዎ ያሉበት ነው።

አንድ ጊዜ አንድ መምህር ደቀ መዛሙራቸው ዋልደባ እሄዳለሁ እያለ ስለአስቸገራቸውም መምህሩም "እመሰ አእመርከ ባቲ ፤ ገረገራ ዋልድባ ይእቲ፡ ካወቅህባት ገረገራ ዋልድባ ናት" አሉት ይባላል ።

አሁንም እርስዎን የምመክርዎ ገዳም ማለት ያሉበት ስለሆነ በኑሮዎ አካባቢዎን ሲአል ከሚያደርጉ ገዳም እንዲሆን ልዎ ቢያደርጉ ገዳም ማለት ይህ ነውና ህሊናዎን ሰብስብ አድርገው ፈተናውን ለመቋቋም ይሞክሩ ።

## የጤና ዓምድ

ከገጽ ፳፫ የዞረ

ታ መነሻ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ከሀኪሞች ምክር ይገኛል ። እንዲሁም ከሥጋ ምግብነት አንዱ የእርያ ወይም የአሳማ ሥጋ በበሽታ ተውሳክ የተሞላ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንኳን ለምግብነት በድንኑም አትንኩ ይለናል "እርያ ሰኰናው ስለተሰነጠቀ ነገር ግን ስለማያሳኳ እርሱ ለእናንተ እርኩስ ነው ሥጋውን አትብሉ በድንኑም አትንኩ ዘዳ. 14 ፥ 8 በተለይ የአሳማ ሥጋ ብዙ በሽታ የሚያመጣ ከመሆኑም ሌላ ሥጋው ብዙ ስብ ስለአለበት በሆድ ውስጥ በቀላሉ ሊፈጭ (ሊሟሟ) ስለማይችል ለሆድ በሽታ ምክንያት ሊሆን ይችላል ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ዓምድ

የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፬

፲፰ወላጆች እንደ ሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም ፤ ወደ
እናንተ እመጣለሁ ። ፲፱ገና ጥቂት ዘመን አለ ከዚህም በኋላ
ዓለም አያየኝም ፤ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ ፤ እኔ ሕያው ነኝና
እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ ። ፳እኔ በአባቴ እንዳለሁ
እናንተም በእኔ እንዳላችሁ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን
ቀን ታውቃላችሁ ። ፳፩ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠ
ብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው ፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደ
ዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ ። ፳፪የአስቆሮቱ
ያይደለ ይሁዳ ፦ ጌታ ሆይ ፥ ለዓለም ሳይሆን ራስህን ለእኛ
ልትገልጥ ያለህ እንዴት ነው ? አለው ። ፳፫ኢየሱስም መለሰ
አለውም ፦ የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል ፤ አባቴም ይወ
ደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ
እናደርጋለን ። ፳፬የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም ፤ የምትሰሙ
ትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም ።

፳፭ከእናንተ ዘንድ ስኖር ይህን ነግሬአችኋለሁ ፤ ፳፮አብ
በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ
ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባች
ኋል ። ፳፯ሰላምን እተውላችኋለሁ ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ ፤
እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም ። ልባችሁ አይ
ታወክ አይፍራም ። ፳፰እኔ እሄዳለሁ ወደ እናንተም እመጣለሁ
እንዳልኋችሁ ሰማችሁ ። የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከእኔ አብ ይበ
ልጣልና ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር ። ፳፱ከሆነም
በኋላ ታምኑ ዘንድ አሁን አስቀድሞ ሳይሆን ነግሬአችኋለሁ ።
፴ከእንግዲህ ወዲህ ከእናንተ ጋር ብዙ አልናገርም ፥ የዚህ ዓለ
ም ገዥ ይመጣልና ፤ በእኔ ላይም አንዳች የለውም ፤ ፴፩ነገር
ግን አብን እንድወድ ዓለም ሊያውቅ ፥ አብም እንዳዘዘኝ ፥ እንዲሁ
አደርጋለሁ ። ተነሡ ፤ ከዚህ እንሂድ ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
የመ.ሣ.ቁ. 1252
የስ. ቁ. 15 82 33
አዲስ አበባ
የመ.ሣ.ቁ. 700
የስልክ ቁ.113455
አሥመራ



www.ethiopianorthodox.org